መስከረም 5-2002 ዓ ም (ሴፕቴምበር 15-2009)

ትዝብት ቁጥር 11

በቅድሚያ አንባብያንን እንኳን ለአዲሱ ዓመት በደህና ደረሳችሁ እላለሁ።

እንደ አቻምናውና አምናው ዘንድሮም ወደ አገራችን ኢትዮጵያ ብቅ ብዬ ነበር።የጉዞዬ ምክንያት ዘመድና አገር ከመጎብኘቱ ባሻገር ቀደም ሲል ለአንድ መቶ ወጣቶች ታቅዶ በመጠናቀቅ ላይ የነበረውን የሙያ ስልጠና ፕሮጀክት ውጤት ለመከታተልና ለማወቅ ነበር።ይህንን ስልጠና በሚመለከት በትዝብት በቁጥር አስር ላይ የገለጽኩት ስለሆነ ዳግም አልመለስበትም፤ሆኖም ግን ስልጠናው ተሳክቶ አንድ መቶ አስራ ስድስት ወጣቶች በሁለት የተለያዩ ቦታዎች ማለትም በደሴ ከተማና በወልድያ በኮምፒውተርና በጸጉር ስራ ሙያ የሚከታተሉትን ኮርስ በመጨረስ የሚገባውን የምስክር ወረቀት ከመረከባቸው በተጨማሪ በተማሩት ሙያ እራሳቸውን ለማስተዳደርና ስራ ለመጀመር የሚያስችላቸው ባጀትና መሳሪያ ተሰጥቷቸው ወደ ስራ ዓለም እንዲገቡ የሚያስችለው እርዳታ ተደርጎላቸዋል።በወጣቱ ዙሪያ ለማበርከት የምፈልገው ነገር ገና አላለቀም።አሁንም የወጣቱ ችግር አልተቀረፈም።ለብዙ ችግርና የምግባር ስብራት ተጋልጦ ይገኛል።ይህን የጋራ ችግር ለመፍታት ወጣቱን በስፖርትና በትምህርት ዙሪያ ለማደራጀትና ለማሰባሰብ አመች ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ ነው።ጥረቱን ፍሬያማ ለማድረግ የግድ አቅም ከፈቀደ በተለያዩ ቦታዎች የወጣቶች ማዕከል ማቋቋም የማይታለፍ ግዴታ ነው።ይህንን በሚመለከተው ተግባር ኢትዮጳያዊው ትልቅ ሚና ቢጫወት የተገባ ነበር ፤ነገር ግን እስካሁን ድረስ በተደጋጋሚ ለተደረገው ጥሪ የተሰጠውን የዝምታ መልስ በማየት በአገር ልጆች ዙሪያ ለቀና ነገር የመሰለፉ ባህልና ፍላጎት የላላ በመሆኑ ከማዘኔ ሌላ የግድ የፈረንጆቹን በር እንዳንኳኳ አስገድዶኛል።ሁሉም ግን ስለአገሩና ስለወገኑ ችግር ሲያወራ እንኳንስ ገንዘቡንና እውቀቱን ቀርቶ ህይወቱንም አሳልፎ የሚሰጥ ይመስላል።አብዛኛው ለሰላማዊው ለውጥ በሚያበረክትው ተግባር ላይ ከመረባረብ ይልቅ ጠመንጃ አንግቦ ጫካ ገብቶ የራሱንና የሌላውን ደም አፍሶ ስልጣን ለመያዝ የሚሯሯጠውን ፋኖ ለመርዳት ሲባዝን ይታያል።አንዳንዱም ጮሌ በእርዳታ ስም ድርጅት አቋቁሞ የራሱን ኑሮ ሲያሻሽልበት ይታያል።በዚህ ወራዳ ተግባር የተሰማራ ለጊዜው እራሱን ብልጥና አዋቂ አድርጎ ቢቆጥር ውሎ አድሮ ለሕግና ለሕሊና ጸጸት መጋለጡ አይቀርም።

አሁንም ቢሆን ተስፋ አልቆርጥም። በሰከነ አዕምሮ በማመዛዘን ነገራት ግልጽ እየሆኑ ሲመጡ የኢትዮጵያኑ ፍላጎትና አስተያየት ወደ ገንቢ አቅጣጫ ይመለሳል የሚል እምነት አለኝ።ወጣቱን ከጅብ አፍ ለማውጣትና ለመርዳት በሚደረገው ሙከራ እውጭ ያለው ኢትዮጵያዊ ከአለፈው በተለየና በተሻለ መልኩ እገዛና ትብብር እንዲያደርግ አሁንም ደግሜ ጥሪ አደርጋለሁ።

ኢትዮጵያ በተለይም አዲስ አበባ ውስጥ በቆየሁበት አጭር ጊዜ ለማየትና ለመስማት የቻልኩት ብዙ ነገር ቢኖርም በጥቂቱ በቦታው ተገኝቶ እንደኔ ላላየውና ላለሰማው ወገን ለማካፈል ቀደም ሲል የገባሁትን ቃል በማክበር እንዳለፉት የትዝብት ዓምዶች አሁንም ለማቅረብ ወስኛለሁ።በአሁኑ ጊዜ ከኢትዮጵያ ውጭ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ ስለአገሩ ጉዳይ የሚከታተልበት ዕድል ከበፊቱ የሰፋና የተሻለ መሆኑ ባይዘነጋም ፣ የትዝብት አምድ ለተለዩ ቡድን ዓላማና ጥቅም ፕሮፓጋንዳ የሚረጭበት ልሳን ሳይሆን የነጻ ሰው አሳብና አስተያየት ከሚንሸራሸርባቸው የተወሰኑ ልሳኖች አንዱ በመሆን በሃቅና በግልጽ ሁኔታዎችን ለማንጸባረቅ ይሞክራል። ዓላማው አገራችንና ወገናችን የሚያልፉበትን ወቅታዊ ሂደት እየመዘገበ ለአሁኑና ለመጭው ትውልድ ለማሳየትና ለማቅረብ ነው።ከተቻለም በክስተቶች ላይ አስተያየትና ትችት ከመስጠት ወደ ኋላ አይልም። ትችትና አስተያየቱ ግን ወደተሻለ አቅጣጫና ውጤት በሚያመራ መልኩ እንጅ ወደከፋና ወደተባባሰ ችግር ወደሚከት አላፊነት የጎደለው ጎጂ ተግባር የሚያስተናግድ አይደለም።

ከአገር ቤት ከተመለስኩ ሁለት ሳምንት ቢያልፈኝም እስከዛሬ ድረስ ድምጼን አጥፍቸ የከረምኩት ልጻፍ አልጻፍ በሚለው የውስጥ ስሜት ክርክር ውስጥ በመግባቴና ለመጻፍም ከወሰንኩ በኋላ በከባቢዬ የተከሰቱ ነገሮች በመኖራቸው እነሱንም ለማካተት በማሰብ ነው።

ወደ ኢትዮጵያ የተጓዝኩት ቅዳሜ እለት በኦገስት አንድ 2009 ነበር።በረራው በሱዳን ዋና ከተማ በካርቱም በኩል አድርጎ ወደ ኢትዮጵያ የሚዘልቅ ነበር።በዚህ በረራ እንደታዘብኩት የተጓዡ ቁጥር ባለፉት ተደጋጋሚ ግዚያቶች እንደማየው ብዙ አልነበረም።የአውሮፕላኑ መቀመጫ ቦታ ከሚይዘው ተሳፋሪ ቁጥር በግማሽ ያህል ባዶ ነበር።ለዚህ

ዋናው ምክንያት  በአሁኑ  በዓለም አቀፍ ደረጃ የደረሰው የኤኮኖሚ መድቀቅ ያስከተለው መሆኑ አይካድም።በውጭ አገር የሚኖረው ኢትዮጵያዊ በብዙ መልኩ ኑሮው ተናግቷል፣ በተለይም በአሜሪካን አገር ከስራ ተባሮ ወይም ተቀንሶ የወር ገቢውን ያጣው፣ከገዛው ቤቱ የተፈናቀለው ቁጥር ቀላል እንዳልሆነ በሰፊው ይወራል።ስለሆነም በያለበት ኑሮን እንዳመጣጡ ከመቀበል ሌላ ምርጫ ስለሌለው ወደ አገሩ ገብቶ ለማረፍና ለመዝናናት የሚያስችል አቅም ያለው እጅግ በጣም ጥቂቱ ነው።አገር ቤት መግባት ብቻ ሳይሆን ገብተው የሚያዩት የቤተሰብ ኑሮና ስቃይ ጤና ስለሚነሳ መሄዱ አይታሰብም። በዚያ ላይ ስለ አገር ውስጥ የሚታየውና የሚሰማው ነገር የሚያርቅ እንጂ የሚጋብዝ አይደለም።የኑሮ ውድነት ከቀን ወደቀን እየጨመረ እንጂ እየቀነሰ ሲሄድ አይታይም። በዚህ ሁሉ ምክንያት ወደ አገር የሚገባው ቁጥሩ ቢቀንስ የሚያስገርም አይሆንም።

ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ተኩል አካባቢ ቦሌ አየር ማረፊያ ደረስን።ከማረፋችን አስቀድሞ የማረፍ ፈቃድ እስኪሰጥ ድረስ በአዲስ አበባ ሰማይ ላይ ትንሽ ማንዣበብ የግድ ነበር።በዚህ አጋጣሚ የከተማዋን መልክ በምሽት ለማየት ዕድል አግኝቻለሁ፣ሆኖም ግን በዛ ድቅድቅ ባለ ጨለማ  በርቀት እንደሻማ  ጭል ጭል የሚሉ  የተወሰኑ የኤሌክትሪክ መብራቶች ከማየት በስተቀር የአንድን ከተማ የምሽት ገጽ ለማሳየት የሚያስችል  ብርሃን አልነበረም።የአዲስ አበባ ከተማ የመብራት እይታ ከካርቱም ጋር ሲነጻጸር ልዩነቱ የሰማይና የመሬት ያህል ነው።የካርቱም ከተማ ለጥ ያለ ሜዳ በመሆኑም ይሁን በመብራቱ ብቃትና ብዛት ከአየር ላይ ደምቃ ትታያለች።ይህም ሆኖ ግን በቦሌ የአውሮፕላን ማረፊያ መሟላትና መኖር የሚገባው የኤሌክትሪክ ብርሃን በመኖሩ ካለምንም ችግር ለማረፍና ወደቀጣዩ ተግባር ለመሰማራት ችለናል።

በእለቱ ፣በተመሳሳይ ወቅት ከተለያዩ አገሮች የገቡ በረራዎች በመኖራቸው የቪዛ መጠየቂያና መቆጣጠሪያ ቦታዎች በሰው ተሞልተው ነበር።በዚሁ እለት ብዙ  ኢትዮጵያውያን  እንግዶች የመጡት ከአረብ አገሮች እንደነበር በአለባበሳቸው ለመገመት ችያለሁ። አብዛኛዎቹ ሴቶች ናቸው፣በዕድሜአቸውም በጣም ወጣቶች ናቸው። ከነዚሁ ውስጥ ከነበሩበት አገር እንዲወጡ የተገደዱ(የተጠረዙ) ብዙ ወጣቶች ይገኙበታል። በማስተናገጃ አዳራሹ ውስጥ ከሚታየው እንግዳ 60% የሚሆነውን የሚሸፍኑት እነዚህ ዕድሜአቸው ከሰላሳ በታች የሆነው  ኢትዮጵያውያን ናቸው። በዕለቱ ከገባው እንግዳ የውጭ አገር ተወላጆች (ፈረንጆችና አረቦች)ከ10% አይበልጡም፤ሌላው ደግሞ ብዛቱ ከ10% የማይበልጠው ለጉብኝትና ለስራ ወይም ለቀጣይ በረራ የመጣ የአፍሪ ዜጋ ሲሆን  የተቀረው 20 % የሚሆነው  ከሰላሳ ዓመት እድሜ በላይ የሚገመት ያለው በውጭና በአገር ውስጥ የሚኖር ኢትዮጵያዊ ነው። እንግዲህ ይህንን የብዛት ሰንጠረዥ ሳወጣ የነበረውን ሕዝብ አንድ ሁለት ብዬ በመቁጠር ሳይሆን የዓይን ግምት በመጠቀም ነው።ሙሉ ለሙሉ ትክክል ነው ብዬ ለመናገር ባልደፍርም የነበረውን አጠቃላይ መልክ ያመላክታል ብዬ አምናለሁ።

በቅድሚያ የተዘጋጀ የመግቢያ ቪዛ ስለሌለኝ የተለዬ ችግር አልገጠመኝም።ይህን ችግር ለመቅረፍ ታስቦ የተዘጋጀ አካል ስላለ የኔ ቢጤው ቪዛ ቢስ እንግዳ ሃያ ዶላር ከፍሎ ለሶስት ወራት ሊኖርበት የሚያስችል ፈቃድ ሊያወጣ ስለሚችል ያንን  ዕድል በመጠቀም ካለችግር ለመግባትና ለመውጣት የሚያስችለውን መብት ለመግዛት ችያለሁ።

ሻንጣየን በካሮሳ ጭኜ ወደ ማስፈተሻው መሳሪያ በማስገባት በቦታው የተመደቡት ሰራተኞች አስፈላጊው ስራቸውን ሲሰሩ በያዝኩት ሻንጣ ውስጥ ትኩረት የሚስብ ነገር በማየታቸው ሻንጣየን ከፍቼ እንዳሳይ በትህትና ጠየቁኝ።እኔም በተጠየኩት መሰረት ተባበርኩኝ።ያ ትኩረት የሳበው ነገር ሌላ ሳይሆን ለእርዳታ የሰበሰብኩት መነጽር ነበር።

ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ሰው ለምንና ለማን እንዳመጣሁት ለማስረዳት ሞከርኩ፤እሳቸው ግን ሊወስኑበት ስለማይችሉ ለበላይ አለቃቸውን ጠርተው ጉዳዩን እንዲመለከተው አደረጉ።እኔም ዳግመኛ ለዚሁ ባለስልጣን ማስረዳት ጀመርኩ።መነጽሮቹ የማየት አቅማቸው ለቀነሰ፣ሊገዙ ለማይችሉ ችግረኞች በእርዳታ የሰበሰብኩት መሆኑን ከዚህም በፊት በተመሳሳይ መንገድ አስገብቸ አገልግሎት ላይ የዋለ መሆኑን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ መኖሩን አውጥቸ በማሳየት ትብብር እንዲያደርጉልኝ በትህትና ጠየኩ።የተሰበሰበው መነጽር ምንም እንኳን አገልግሎት የሰጠ ቢሆንም ለጋሹ የመነጽሮቹን ደህንነት፣በመጠበቅና በማደስ እንዲሁም መጠናቸውን በመመርመር ለአገልግሎት ብቁ መሆናቸውን በተጨማሪም  ለእያንዳንዱ መነጽር መያዣና የመጠን ማረጋገጫ ካርድ አዘጋጅቶ አስረክቧል፤ይኸው ድርጅት ከዚህ ቀደምም ተመሳሳይ እርዳታና አስተዋጽኦ አድርጎልኛል።የሚገርመው ነገር በመነጽር ስራ ውስጥ የተሰማራ፣ ለተመሳሳይ እርዳታ በቂ ሁኔታ ውስጥ ያለ በጣም የማውቀው ኢትዮጵያዊ እንዲተባበር ጠይቄው ቃል ከገባልኝና  ብዙ ከቀባጠረ በኋላ ፣ደጋግሜ ብጠይቀውም ዛሬ ነገ እያለ ከነጭራሹ ድምጹን አጠፋ።።ይህ በሱ ላይ ብቻ የሚንጸባረቅ በሽታ ሳይሆን

በአብዛኛው ላይ የሚታይ ከተግባር ጋር ያልተዛመደ ባዶ የአገር ፍቅር ስሜት ነው። በምኖርበት ከባቢ ውስጥ የመነጽር መሸጫ ሱቅ ያላት ኢትዮጵያዊ ያልሆነችው ፈረንጅ ግን ያቀረብኩላትን ጥያቄ በደስታ ተቀብላ ይኸው በተደጋጋሚ እርዳታዋን ለግሳለች፤ ለወደፊቱም ላለማቋረጥ ቃል ገብታለች።እስከአሁን ድረስ በእሷ በኩል በተገኘው እርዳታ ከመቶ ሃምሳ በላይ የሚሆኑ የማየት ድክመት ያለባቸው ፣ገዝቶ ለመጠቀም የማይችሉ አባት አርበኞችና አዛውንቶች፣ ጎልማሳና ወጣቶች፣ተጠቃሚዎች ሆነዋል።

ታዲያ ለዚህ ተግባር የተሰበሰበውን መነጽር ማስገባት አትችልም በማለት ባለስልጣኑ ወሰኑ።የሰጡት ምክንያት ቢኖር መንግስት አሮጌ ዕቃ እንዲገባ አይፈቅድም፤ ካመጣህ አዲስ ዕቃ ይዘህ ና የሚል ነበር።እኔም ሙሉ በሙሉ ባልቃወምም፣አዲስ የማገኝበት ሁኔታ እስኪፈጠር ድረስ በምናገኘው የተጠቃሚውን ችግር መቅረፍ ይኖርብናል እንጂ ችግሩ በከፊልም ቢሆን ሳይነካ ይኑር ብሎ መወሰን በችግረኞቹ ላይ መፍረድና መወሰን ይሆናል።ደግሞም ለማኞች ሆነን ለጋሹን ይህንን ካልሰጠህ ብለን ልናስገድድ አንችልም።ከዚህ በፊት የገቡት መነጽሮች ችግረኞቹን ጠቀሙ እንጂ አልጎዱትም። አይገባም ማለት ተጠቃሚውን እንደተደናበርክ ኑር ማለት ነው በማለት እልህና ብስጭት የተሞላበት ቃል ስናገር በአጠገቤ ያሉት ቤተሰቦቼ ነገሩን ለማለሳለስና ለማብረድ ሞከሩ ፣እኔም የይገባኛል ክርክሬ ወደ ልመናና መለማመጥ ተለውጦ የባለስልጣኑም አቋም ተቀይሮ ይዤ ለመግባት ቻልኩ።የሚያስገርመው ነገር ግን መንግስት አሮጌ ዕቃ እንዲገባ አይፈቅድም እየተባለ፤ ከባቢና የሰው ጤና የሚበክል ጭስ የሚተፉ፣ በሌላው አገር መንገድ ውስጥ መታየት የማይገባቸው አሮጌ መኪናዎች ብዙ ቀረጥ እየተከፈለባቸው እንዲገቡ መፈቀዱ ነው።እነዚሁ በመጡበት አገር መጣያ ያጡ መኪናዎች ለሽያጭ የሚጠየቅባቸው ዋጋ በአዲስነታቸው ያልተጠየቀባቸው ነው። በአዲስና በተሻሉ መኪናዎች ላይ የተጣለው ከፍተኛ ቀረጥና ያለው የመጓጓዣ እጥረት ችግር የነዚህን ለአደጋ የሚያጋልጡ፣ አገልግሎታቸውን የጨረሱ አሮጌ መኪናዎች ዋጋና ገበያ ከፍ አድርጎታል። አገር የሚበክል፣በቀረጥ ከማስገባት አገር የማይጎዳው፣ ሰውንም ለአደጋ የማያጋልጠው አዲሱ መኪናም ሆነ ሌላው መገልገያ መሳሪያ ሲሆን ከቀረጽ ነጻ አለያም በትንሽ የቀረጥ ክፍያ እንዲገባ ማድረግ ያለውን የሕዝብ ችግር ሊያቃልለው ይችላል ብዬ አስባለሁ።መታየት ያለበት ከቀረጡ ክፍያ ባሻገር ከባቢና ሰው ሳይጎዳ ሊሰጥ የሚችለው አገልግሎት ነው። ያለለት ሕዝብ ከባቢውን ለመንከባከብ በሚረዳው ተግባር ሲተባበር መንግስት ድጋፍና ማበረታቻ ያደርግለታል። በሌሎች አገሮች በመኪና ዙሪያ የሚደረገውን መሻሻልና የሚከተሉትን የመንግስታት መመሪያ ማዬትና መስማቱ ትምህርት ይሰጣል።

በታክሲ ወደቤት ስሄድ በቂ የመንገድ ላይ መብራት አልነበረም። በአገር አቀፍ ደረጃ የተከሰተው የኤሌክትሪክ ሃይል ድክመት የተነሳ መብራት በወረፋ ከሆነ ወራቶች አልፈዋል።ዛሬ የመብራት እድል ያገኘ ነገ አይኖረውም።እንግዲህ በዚህ መልኩ ጉዞዬ መብራት ያለውንና የሌለውን ሰፈር እያቋረጥኩ ነበር።የኤሌክትሪክ መብራት እንድም ተረኛ በመሆን አለዚያም የግል ጀኔሬተር በመግዛት ይገኛል፤ ለዚያ ያልታደለው ግን በባትሪ ወይም በዲናሞ ተሞልታ ጊዜያዊ ብርሃን በምትሰጥ ተንቀሳቃሽ የእጅ መብራት ወይም በሻማ ጨለማውን ለመስበር ይሞክራል።

ችግሩን በቅድሚያ ስለማውቅ አምናም ያለፍኩበት ስለሆነ ከአለሁበት አገር ከመነሳቴ በፊት በስማ በለው ባገኘሁት ማሳሰቢያ የካምፕ መብራት ይዞ መሄዱ እንደሚረዳ በማመን ተዘጋጅቸበት ነበር።የሚገርመው ነገር ግን በተመሳሳይ ደረጃ አገልግሎት የሚሰጡ መብራቶች ከተማውን አጥለቅልቀው እኔ ከገዛሁበት ዋጋ በጣም ዝቅተኛ በሆነ ተመን በገባዬ ላይ መዋላቸውን ሳይ በከፍተኛ ዋጋ ገዝቼ ተሸክሜ መውሰዴ ሳይከነክነኝ አልቀረም።ሆኖም ግን አገልግሎቱ ሲታይ ካወጣሁት ገንዘብ በልጦ አገኘቸዋለሁ።

በብዛት መብራት የሚጠፋው ከጧት አስራሁለት ሰዓት ጀምሮ እስከምሽቱ ሶስት ሰዓት ተኩል ስለሆነ እቤት ስደርስ የኤሌክትሪክ መብራት በመመለሱ ከቤተሰብ ጋር ለመተያየትና ቀሪውን ጊዜ በብርሃን ውስጥ ተቀምጦ ለመጫወት ችያለሁ።

የዚህን በኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ዙሪያ በተመለከተ ጉዳይ ላይ ከአንዳንድ ባለሙያዎች ጋር ሳልወያይ አልቀረሁም።በዚሁም የነበረኝ አመለካከት ሊለወጥ ችሏል።እሰማ የነበረው ተባራሪ ወሬና በሃቅ ላይ ያልተመሰረተ አሉቧልታ እንደሆነ ካገኘሁት የባለሙያዎች አስተያየት ለመገንዘብ ችያለሁ፤ ይኸውም የአገሪቱ የኤሌክትሪክ ሃይል በመንግስት ለውጭ አገር እየተሸጠ፣ግድቦች ደለል ሲወርሳቸው ዝም ተብሎ እየታዬ በአገሪቱ ላይ ለደረሰው ችግር ዋና ምክንያትና ተጠያቂ መንግስት ነው የሚል ነበር።በአገኘሁት ግንዛቤ ግን ችግሩን በማሶገድ ደረጃ ምንም እንኳን ቅድመ ጥናት የማድረግና እርምጃውን በማፋጠን ደረጃ የመንግስትና የሚመለከተው ክፍል ድክመት ቢያሳይም ከላይ የተገለጸው ከእውነት የራቀ ለመሆኑ ጭብጥ ማስረጃዎች በዘርፉ ከተሰማሩ ባለሙያዎች ለመስማት ችያለሁ።

1ኛ በተከዜና በግልገል ጊቤ ወንዝ ላይ በመሰራትና አገልግሎት ለመስጠት የቻሉት የሃይል ማመንጫ ሃይሎች ከአገር አልፎ ለውጭ አገር የሚተርፍ ሃይል ለማምረት  በአሁኑ ደረጃቸው ብቃት የላቸውም።መጠናቀቁ የሚነገርለት ግድብ የሚያመርተው የሃይል መጠን ከሰባ አምስት ሜጋዋት በላይ አይበልጥም፤ይህ ለምን ያህል ከባቢ፣ ለስንት ቤት፣ድርጅትና ፋብሪካ ሊበቃ እንደሚችል ለባለሙያው የተሰወረ አይደለም።እንኳንስ ከኢትዮጵያ ተርፎ ለውጭ ገበያ ሊውል ቀርቶ ለኢትዮጵያም ውስጥ ፍጆታ አንድ አስረኛውን እንደማይሸፍን ባለሙያዎቹ ይናገራሉ።

2ኛ እስከዛሬ ድረስ አገልግሎት ሲሰጡ የነበሩት የሃይል ምንጮች የሚያመርቱት ሳይጨምር የኤሌክትሪክ ሃይል ፈላጊው የመኖሪያ ቤት፣ የድርጅትና፣የፋብሪካ መጠን ጨምሯል።የፍላጎትና ያቅርቦት አለመጣጣም ተከስቷል ማለት ነው፤ሌላ አማራጭ በሌለበት አገር ደግሞ የተወሰደውን የወረፋ አገልግሎት እንደ አንድ  መፍትሄ አድርጎ ለመውሰድ ያስገድዳል።

3ኛ የቆዩትም ሆኑ አዲሶቹ የማመንጫ ግድቦች የሚተማመኑት በውሃ ነው።ዝናብ ካልጣለ ግድቦቹ ባረፉባቸው ወንዞች በቂ ውሃ አይኖርም፣ያም ማለት በውሃው ብዛትና ፍጥነት ተሽከርክረው የኤሌክትሪክ ሃይል ሊፈጥሩ የሚችሉት ተርባይኖችና ጀነሬተሮች  ማምረት አይችሉም፤ ቢችሉም  ዝቅተኛ ይሆናል ማለት ነው።በመደጋገም የደረሰው የዝናብ እጥረት ለድርቅና ለእርሃብ እንደዳረገን ሁሉ የኤሌክትሪክ ምርቱንም እንዳቀጨጨው መካድ አይኖርብንም። በውሃ እስከተማመንን ድረስ ፣ በተፈጥሮ ለውጥ የተነሳ የውሃ  እጥረት በተደጋጋሚ ስለተከሰተ የግድቦች መብዛት ዋስትና ሊሆን እንደማይችል መረዳት አለብን። ችግሩ በማንኛውም መንግስት አስተዳደር ሊከሰትና ሊኖር እንደሚችል ማወቅ አለብን ።እንኳንስ የፖለቲካ ድርጅቶች ቀርተው ሃዋርያትም ስልጣን ቢይዙ ሊወገድ የሚችል ችግር አይሆንም።ለዚህ መፍትሄ የሚሆነው ነገር አማራጭ የሃይል ማመንጫ ዘዴ ሲተካ ነው።የንፋስ፣የጸሃይ ወይም የኑክሌር ማመንጫ ሌላው ሃብታም አገር የሚገለገልበትና ለመገልገልም ፊቱን እያዞረ የመጣበት ብዙ ሃብትና ዕውቀትን ፍላጎትና ጥረትን የሚጠይቀው የዘመኑ የሃይል ማመንጫ ዘዴ ነው።ለዚህ አይነቱ ብቃት ፍላጎት ብቻ ሳይሆን አቅም ይጠይቃል። ገንዘብን፣እውቀትን፣ፍላጎትንና፣ጥረትን ይጠይቃል። ለዚህ ደግሞ አልታደልም።በስድብና በአሉቧልታ የሚወገድ ችግር አይደለም።

 የችግሩ መኖር ግን ለአንዳንዱ ነጋዴ የጥቅም በር ከፍቶለታል።ቀደም ሲል በሁለት ሽህ ብር ይሸጥ የነበረው አነስተኛ ጀኔሬተር አሁን ከሰባት ሽህ ብር በላይ ይጠየቅበታል።በዚህ ችግር ዙሪያ የሚያለቅስም የሚስቅም ወገን አለ።የጀኔሬተሩ ነጋዴ ችግሩ ቢቀጥል ደስታው ነው።በሌላ የንግድ ዘርፍ የተሰማራው አቅም የሌለው  ለምሳሌ አነስተኛ  ቡናቤት፣ምግብ ቤት፣ክሊኒክ፣የጸጉር/ ባርቤሪ/፣ወፍጮ ቤት ...ወዘተ ስራቸውን ከማቆም ሌላ አማራጭ የላቸውም።እንግዲህ እነዚህ አነስተኛ ድርጅቶች ከወር ውስጥ ለአስራ አምስት ቀናት ስራፈቶች ይሆናሉ ማለት ነው።መንግስት  ችግሩን አጢኖና ከግምት አስገብቶ መከፈል የሚኖርባቸውን ግብር ላይ አስተያዬት አላደረገላቸውም።

በዬአንዳንዱ የንግድ ድርጅትና ሱቅ በር ደጃፍ ላይ ካርቶን ተሸፍኖ ከሚንደቀደቀው አነስተኛ ጀኔሬተር የሚወጣው ድምጽና ጭስ ለከባቢውና በአላፊ አግዳሚው ሰው ጤና ላይ ሊያደርስ ለሚችለው ጉዳት ትኩረት የሰጠው የለም።ጤና ጥበቃም ሆነ ማዘጋጃ ቤት በጉዳዩ ያሰቡበት አይመስልም።በእርግጥ በዚህ ችግር ውስጥ እየማቀቁ መኖር ይሻላል ማለት አይደለም።ለችግሩ የሚሰጠው መፍትሄ ዘላቂና አስተማማኝ በሆነ መልኩ ቢሆን እንደሚሻል ለመጠቆም ነው። የመብራት ሃይል መስሪያ ቤት ከከባቢው ነዋሪና የድርጅት ባለቤቶች  ጋር በመመካከርና በመረዳዳት ብቃትና ዋስትና ያለው ተለዋጭ የኤሌክትሪክ ሃይል ሊሰጥ የሚችል ጀኔሬተር የሚተካበትን መንገድ ቢፈልግ አንዱ መፍትሄ ሊሆን ይችላል።ሌላው ቢቀር በአንድ ከባቢ የሚገኙ የድርጅት ባለቤቶች በህብረት  አንድ የተሻለ ገዝተው  በጋራ ቢጠቀሙ ውጤቱ የተሻለ ነበር።ዳሩ ግን አብሮና ተባብሮ የገጠመን ችግር ለማሶገድና አብሮ ለመስራትና ለመጠቀም ባህልና ፍላጎቱ ስለሌለ የመጣውን ችግር በግል ለመጋፈጥ ሁሉም በየፊናው ሲባዝን ይታያል።በዚህ አይነቱ አካሄድ ደግሞ የተሻለ ውጤት አይገኝም፤ቢገኝም ጊዜያዊና ውስን ነው።

በጣም የሚገርመው ነገር ቢኖር በዚያ ምሽት የሻማ መብራት ብቻ በማብራት በራቸውን ወለል አድርገው በመክፈት ደንበኛ ለማስተናገድ የሚጠባበቁ የወርቅ መሸጫ ሱቆች መኖራቸው ነው።ይህን ሲያዩ የኢትዮጵያ ህዝብ ምንም ቢቸገረው አመጽን ተጠቅሞ ለዘረፋ እንደማይነሳና ጨዋ ሕዝብ መሆኑን ያረጋግጣል።በሌሎች የአፍሪካና የላቲን አሜሪካ አገሮች የሚታየውና የሚሰማው ከዘረፋ ጋር የተያያዘ ወንጀል በዚህ አመቺ ሁኔታ አለመከሰቱ የህዝቡን ስነምግባር ያሳያል። ለመሆኑ ግን  ችግሩና መከራው እየበዛ ሲሄድ ይህ ጨዋነት ሳይለወጥ ይዘልቅ ይሆን?

   በዚህ መስከና ሌላውንም አገሪቱ የተዘፈቀችበትን ችግር ለማሶገድ የመንግስትና የሕዝብ ትብብር ያስፈልጋል።ሌላው ቀርቶ የግለሰቦች አስተዋጽኦ ከፍተኛ ድርሻ አለው።የሚያሳዝነው ነገር ግን አንዱ በአንዱ ላይ ችግሩን እየለጠፈ ችግሩ ሳይወገድ እንዲኖር ማድረጉ ነው።እንደ አጋጣሚ ያገኘሁትና ስለችግሩ የተወያየሁት በኤሌክትሪካል ኢንጂነሪንግ ከፍተኛ

ትምህርት ቀስሞ በሙያው በመስራት ላይ ያለው ወጣት ምሁር “በኢትዮጵያ ብር በሚከፈለኝ ደመወዝ የምፈልገውን አይነት ኑሮ ለመኖር ተስኖኛልና እባክህ በምትኖርበት አገር የስራ እድል ካለ ኢንፎርሜሽን ፈልገህ ላክልኝ” ብሎ ሲጠይቀኝ፣እራሱ ሰውየውና ጨዋታው ኮረንቲ የያዘኝ መስሎ ተሰማኝ፣ ሰውነቴን ወረረው፣አናደደኝ። በውጭ አገር የስራው እድል የጠበበ መሆኑንና  በአገሩ ላይ በያዘው ስራና የአላፊነት ቦታ የአገሪቱን ችግር ለመቅረፍ በሚያስችለው ተሳትፎ  አላፊነትና ግዳጅ እንዳለበት ስነግረው ቅር ተሰኝቶ ተለያየን፣ከዛም በኋላ ለመገናኘት የነበረን እቅድ ከሸፈ። ይህ ሰው ከመንግስት ጋር የሚያቃርነው ተግባር ላይ አልዋለም፤ ድምጹን አጥፍቶ የሚኖር ሰው ነው። በገቢም ደረጃ በአገሪቱ ውስጥ ጥሩ ደመወዝ ያገኛሉ ተብለው ከሚገመቱት ባለሙያዎች አንዱ ነው። የተጠናወተው ነገር ያልጠግብ ባይነትና የብሔራዊ ስሜት መላላት በሽታ ነው።መስራት የሚችለው ኢትዮጵያዊ አገሩን እየጠላ ሲሸሽ ሌላው የውጭ አገር ዜጋ በቦታው እየተተካ ሲጠቀም በዘላቂ ሂደት አገርን ጥገኛ አድርጎ እንደሚያስቀር መታሰብ አለበት። እያንዳንዱ ሰው ለሚፈልገውና ለሚመኘው ነገር ልክና ገደብ ካላበጀለት፣ ባለው ሳይረካ ፣የመንፈስ መረጋጋት ሳያገኝ እንደናወዘ ይኖራል።ይህ አዝማሚያ በዚህ ግለሰብ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን በአብዛኛው ያገሪቱ ዜጋ ጭንቅላት ውስጥ የሚሽከረከር በሽታ ነው።

በእርግጥ አንድ ሰው ከአገሩ ወጥቶ መኖር የለበትም አይባልም።ከቻለ ልቡ ካሰበበት ቦታ የመሄድ መብቱን ማንም ሊገፈው አይችልም።መታየት ያለበት መብትና ግዴታንም ሲያካትት ነው።የግል ጥቅምን ሲያሳድዱ ለሌላው ሰብአዊ ፍጡር በተለይም ለቁም ነገር ላበቃ አገርና ህብረተሰብ ውለታውን መክፈልና መጥቀም እንደሚገባ የውዴታ ግዴታ መኖሩን በቅድሚያ ማወቅ ይገባል።ሁሉም ካገር ለመውጣት የሚያስብ ሰው አንድ አይነት ምክንያት አለው ማለት አይደለም።ሰብአዊ መብቱ ሲገፈፍ፣በአገሩ ጉዳይ ላይ ባይተዋር ሲሆን፣የሃሳብና የተግባር ተሳትፎው ሲገደብና ሲገታ፣በትውልድ ሃረጉና በፖለቲካ እምነቱ ሲታሰርና ሲንገላታ፣ የፈለገውን የመደገፍ ያልፈለገውን ደግሞ የመቃወም መብቱ ሲጣስና ሲረገጥ፣ ስልጣን ላይ ለተቀመጠ ሃይል አጫፋሪና ደጋፊ ባለመሆኑ የተነሳ የስራ ዕድል ሲነፈገው ወይም ከስራው ሲባረር፣ በአገሩ ምድር ላይ የዜግነት መብቱ ተገፎ ለሌላው የበታች ሆኖ እንዲያድር ሲገደድ፣ በአጠቃላይ እንደ ነጻ ሰው ለመኖር የሚችልበት ሁኔታ ሲጓደልበት መሄድ ከሚችልበት ቦታ ሄዶ ከሚደርስበት መከራ  አምልጦ ለመኖር የሚችልበት ዕድልና አጋጣሚ ካለ ለምን ትወጣለህ አይባልም። የሚባለው እንኳን አተረፈህ ነው።ያጣውን ሰላማዊ ኑሮ ለመኖር ሲችል ማየቱ ደስ ያሰኛል።እንዲህ አይነቱ ሰው በአገሩ ውስጥ ሲኖር ያሳለፈው ስቃይ ችግሩ በሚወገድበት መንገድ ለመሰለፍ ወደኻላ አይልም።ለዚህ ዓላማ ግን የሚወጣው በጣም ጥቂትና የተወሰነ ነው።በሌላ መልኩ ግን አወጣጡ በአገሩ ላይ ምንም ጉዳትና መንገላታት ሳይኖርበት  በተሰማራበት የግልም ሆነ የመንግስት ስራ፣በቀሰመው ሙያና ችሎታ አገርና ወገኑን የሚያገለግልበት ነጻ መድረክ ኖሮት ያንን ረግጦ  ለበለጠ ደመወዝና ፍቅረ ነዋይ ከሆነ ባገኘው አጋጣሚ ወጥቶ የስደት ኑሮ የሚሻው ከትዝብት ላይ ይጥለዋል። በዚህ መንገድ የወጡ አብዛኞቹ የሚፈልጉትን ሳያገኙ ባክነው የቀሩ ጥቂቶች አይደሉም።ለመጨመር  የምፈልገው አንድ ነገር ቢኖር፣ኢትዮጵያ ያለፈችበትንና በማለፍም ላይ ያለችበትን መንገድ ያለፉ ብዙ አገሮች አሉ።አብዛኛዎቹ መከራን አልፈው የሰላምና የእድገት ባለቤቶች ሆነዋል።ለዚያ ዕድል የበቁት ግን ተከፋፍለውና እርስ በርሳቸው እየተጨፋጨፉና አገር ጥለው እግሬ አውጭን ብለው በመሸሽ አይደለም።በከፈሉት መስዋዕትነት ነው።በተለያዩ ዘዴ የሕዝባቸውን አመለካከትና ኑሮ ለመለወጥ በሚያስችለው መንገድ በመሳተፍ ነው።ተሳትፎ ብዙ መልክና አቅጣጫ አለው፤ የግዴታ በአመጽ ብቻ መካፈል አይደለም። በሰላማዊ የትግል ሜዳም ብዙ ድሎች ማስመዝገብ ይቻላል። በሰላማዊ የዲሞክራሲ ትግል መድረክ ተሰልፎ ፣ለጥቅም ወይም ለሚገጥመው ችግርና ስቃይ ሳያጎበድዱ እጅ ለእጅ ተያይዞ በመጓዝ የማታማታ የድል ባለቤት መሆን ይቻላል።እህል ተወደደ ወይም ጠፋ ብሎ ማውራት ወይም መቃወም ቀላል ነው ችግሩ ግን እንዲወገድ ከተፈለገ በመስኩ ተሰልፎ ምርት የሚጨምርበትን መንገድ መሻቱ ተገቢ ነው።ሌላ ሌላውም እንዲሁ።

እያንዳንዱ ለራሱ አድራጎት ዳኛ ሆኖ ፍርዱን ቢሰጥበት ስለሚሻል የራሴን አስተያየት እዚህ ላይ በማቆም ወደ ሚቀጥለው እርዕስ አመራለሁ።

## በኤኮኖሚው ዙሪያ

በአገሪቱ ውስጥ ይታይ የነበረው እንቅስቃሴ ተዳክሟል።በዓለም አቀፍ የደረሰው ውዝግብና ክስረት በኢትዮጵያ ላይ ከባድ ክንዱን አሳርፏል።የአገሪቱ ከፍተኛ ገቢና ለግንባታ የሚውለው ገንዘብ ከውጭ አገር መንግስታትና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች የሚገኘው ብድርና እርዳታ ነበር። አገራት በደረሰባቸው ቀውስ እንኳንስ የሌላውን አገር ኤኮኖሚ ሊደግፉ ቀርቶ የራሳቸውንም ለማዳን ተስኗቸው ከፍተኛ ጥረት እያደረጉ ነው።እንደ ኢትዮጵያ ዝቅተኛ የኤኮኖሚ አቅም ባላቸው አገሮች ላይ የደረሰው ስብራት የሕዝቡን ኑሮ ከድጡ ወደ ማጡ ከቶታል።የዕቃና የምርት እጥረት መኖር የዋጋ ግሽበት አስከትሏል።የውጭ አገር ምንዛሪ ባለመኖሩ በዛ ላይ የተንጠለጠሉ ድርጅቶችና የስራ መስኮች መንቀሳቀስ ተስኗቸው

ለመዘጋትና ሰራተኛ ለማሰናበት ተገደዋል።ከውጭ አገር ተገዝቶ ይገባ የነበረው የመድሃኒት፣የፋብሪካ መሳሪያ መለዋወጫ፣ለግንባታ ስራ ማካሄጃ የሚያስፈልግ ዕቃ...ወዘተ እጥረት በመከሰቱ በብዛት የተጀመረው በእንጥልጥል ቀርቷል። በተለይም መድሃኒት በመጥፋቱ በቀላሉ ሊወገድ የሚችለው በሽታ እየበረታ በብዙ ሕይወት ላይ የሞት አደጋ አድርሷል። በኤሌክትሪክና በጥሬ ዕቃዎች አቅርቦት ማነስ የተነሳ የሲሚንቶ እጥረት ተከስቶ የተጀመሩ ቤቶችና ሕንጻዎች ስራቸው አዝግሟል።ተሰርተው ያለቁትም ተከራይ አጥተው ባለቤቶቹ ባለ ዕዳ ሆነዋል።

በአጠቃላይ ሁሉም ነገር ተወዷል።እንኳንስ ከውጭ አገር ተገዝቶ የሚመጣው ሸቀጣ ሸቀጥና ምርት በአገር ውስጥም የውጭ ምንዛሪ ሳይጠይቅ የሚመረተው ምርት በቀላሉ የሚያገኙትና ገዝተው የሚጠቀሙበት አልሆነም።

በተደራራቢ ችግርና እጥረት የተነሳ "የነጻ ገበያ" በሚለው መርሆ ብዙ የሚወራለት የኤኮኖሚ መመሪያ/ፖሊሲ/ በተግባር "የነጻ ዘረፋ"በሚል ተተክቶ ሕዝብ እያለቀሰ ነው።በገበያው ዙሪያ ያልተረጋጋ ሁኔታ በመኖሩ የነገን ሳይሆን በጧትና ከሰዓት በኋላ መካከል የሚኖረውን የዋጋ ተመን ለመናገር አይቻልም።ጧት ሃምሳ የነበረው ማታ መቶ ሆኖ ያድራል።

በመኖሪያ ቤትና በቦታማ ዙሪያ የሚጠራውን ዋጋ ሲሰሙት ያለሁት ኢትዮጵያ ነው ወይስ ጃፓን ወይስ አውሮፓ ያሰኛል።እርግጥ በቤት ግንባታ ላይ ብዙ ለውጥ ይታያል።ሆኖም ግን ሊገዛና ሊኖር የሚችለው በጣም ጥቂቱ ነው።የሕንጻና የመኖሪያ ቤት ግንባታ የሚያካሂዱ የተለያዩ ድርጅቶች አሉ።በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በልዩ ልዩ ቦታዎች ታላላቅ የህንጻ ስራ በማካሄድ ላይ ናቸው፤ሆኖም ግን ለመሸጥ የሚጠሩት ዋጋ ከአቅም በላይ ነው።በአገኙት ቦታ ላይ ምንም ክፍተትና ለኑዋሪው የዓይን ማረፊያ የሚሆን የአትክልት ቦታና መዝናኛ ብሎም የልጆች መጫወቻ ሳያካትቱ እያንዳንዷን ካሬ ሜትር ቦታ በመጠቀም ለአደጋ የተጋለጡ የተጠጋጉ ህንጻዎች ሲሰሩ የከተማ ልማቱም ሆነ ማዘጋጃ ቤቱ የወሰደው እርምጃና ያወጣው መመሪያ የለም።ብዙ ሕንጻዎች መሰራታቸው ባይካድም በጥራታቸውና በምቾታቸው ግን ፈተና ቢወጣ የሚያልፉት በጣም ጥቂቶቹ ናቸው።የማድቤትና የሽንት ቤት ጠረን ማሶገጃ (ventilation)የሚባል ነገር እንግዳ ነው።ያው በርና መስኮት እየከፈቱ ማራገብ ነው። ለመታዘብ በብዛት ሕንጻዎች የተገጠገጡበትን የካዛንችስን ከባቢ ገብቼ ተመልክቻለሁ።ካለማጋነን የየአንዳንዱ የሕንጻ ቅርበት በመስኮት ዕቃ ሊቀባበሉበት የሚያስችል ሲሆን ከመንገድ ፍለፊት ከሚሰሩት ሕንጻዎች በስተቀር አብዛኛዎቹ በብርሃን ማነስ የተነሳ ውስጣቸው ጨለማ ነው፣የግድ ቀንና ማታ መብራት ማብራት ያስፈልጋል። በዚህ ዙሪያውን በህንጻ በታጠረ መኖሪያ ቤት የሚኖር ሰው ቤት ገዛሁ ከማለት ይልቅ ብዙ ሚሊዮን ገንዘብ ያፈሰሱበት የግል እስር ቤት ገዛሁ ቢል ይሻላል።ከፊቱ ግምብ፣ከኋላው ግምብ፣ከጎኑ ግምብ ሆኖ የሚያየው ሰማይ ከሆነ ምኑ ከስር ቤት ይሻላል? ከእነዚህ በብዛት እንደችቦ ተቃቅፈው በቆሙት ህንጻዎች መሃል አያድርስና በአንዱ ላይ አደጋ ቢደርስ እንደ ዶሚኖ ተያይዞ ከመገርሰስ አይተርፍም።በዚህ መልክ ለሚሰሩት የአፓርትመንት መኖሪያ ቤቶች በዋጋ ደረጃ ግን አፍ ሞልቶ ብዙ ሚሊዮን የሚጠራባቸው ናቸው።በጣም የሚያስገርመው ነገር በሚመሰረቱትና በሚገነቡት መኖሪያ ሰፈሮች ከባቢም ሆነ በከተማው ዙሪያ የህዝብ መናፈሻና ለከባቢው ውበት የሚሰጥ የዛፍ ተክል አለመታየቱና አለመታሰቡ ነው።

አንድ ቋሚ ነገር ሲሰራ በተለይም የሕንጻ ስራ ቢያንስ ቢያንስ ለሃምሳና ከዚያም በላይ ዓመታት አገልግሎት ይሰጣል በሚል ግምት መሆን ይኖርበታል።በዚህም የጊዜ ተመን የህብረተሰቡ ኑሮና የአገሪቱ እድገት፣የከተማው መንገድና መጓጓዣ፣ ልዩ ልዩ ያገልግሎት መስጫ መስመሮች ሊዘረጉበት የሚችሉበት የተመቻቸ ሁኔታ አስቦ ማዘጋጀት የግድ ነው፣በየጊዜውም እያፈረሱ ከመገንባት ያድናል። የሚታየው ሂደት ግን በአለው አጋጣሚና የሕዝብ ጥያቄ ምክንያት የረባ ያረባ ነገር እየሰሩ ገንዘብ ማግበስበስ ነው።ለዚህ መድሃኒቱ ቦታና ቤት ለመግዛት የሚያስበው ወገን የሚፈልገው እንዲሟላለት መጠየቅ ይኖርበታል።ያ ካልሆነ ግን በቤት ሰሪዎቹ ፍላጎትና ምርጫ የሚቀርብለትን ባይገዛ የተሻለ ነው።በተጨማሪም በአዲስ አበባ ከተማ ገና ብዙ ያልተነካና፣ በአዲስ መልክ የመኖሪያ ቤት ስራ የሚጠይቅ ከባቢ አለ።ከተማው ገና ብዙ የሚቀረው አለ።ዘጠና ከመቶ የሚሆነው የከተማ ቦታ መልኩን አልቀየረም፤በነበሩት ደሳሳና ቁሻሻ ሰፈሮች የተዋጠ ነው።ወደፊት ለውጥና ለዋጭ ይፈልጋል።

በተጨማሪም አሁን በግንባታ ዙሪያ የሚታየው የመሳሪያና የዕቃ፣በተለይም የሲሚንቶ አጥረትና ከዚያውም ጋር የተያያዘ የዋጋ መጠን ከጊዜ ጋር ነባሮቹና አሁን በመሰራት ላይ የሚገኙት አዲሶቹ ፋብሪካዎች ሙሉ ለሙሉ ማምረት ሲችሉ ገበያው ሊረጋጋና ዋጋውም ሊቀንስ ይችላል ተብሎ ይጠበቃል።

በተጨማሪም መንግስት ወይም የከተማው አስተዳደር የግዴታ ትላልቅ ሰማይ ጠቀስ ፎቅ ካልተሰራ ብሎ በአቅሙ መሰረት መለስተኛ ፎቅና የመኖሪያ ቤት ሊሰሩ የሚፈልጉትን፣ለከተማው እድገትና ንጽህና ሊያበረክቱ የሚችሉትን ዜጎች መግፋትና ተስፋ ማስቀረጥ አይኖርበትም።አለበለዚያ ያ ከተማ ጥቂት ሚሊየነርስ የሚኖሩበት ከተማ ይሆናል

ማለት ነው።መታሰብ ያለበት እድገቱ ከሕዝቡ አቅም ጋር የተዛመደ መሆኑ ነው።የቁሻሻ ሰፈር ሳይነካ ይኑር ማለት ሳይሆን፣የግዴታ ሰማይ ጠቀስ ሕንጻ ብቻ መሆን የለበትም ለማለት ነው።ደረጃን የጠበቀ ለውጥና እድገት ጥቂቶችን ብቻ ሳይሆን ብዙሃንን ያሳትፋል።

ሌላው በመንግስት በኩል የሚሰራው የኮደሚኒየም መኖሪያ ቤት በጥራቱና በምቾቱ የተዋጣለት ነው ባይባልም ከደሳሳ የቀበሌ ቤቶች የተሻለ ነው።ይህ በውጭ አገር ድርጅቶችና መንግስታት እርዳታና ብድር የሚሰራው ቤት አጀማመሩ አቅም የሌለውን ደሃ ሕዝብ የዕድሉ ተካፋይ ለማድረግና የከተማውንም ውበት ለማሻሻል ታስቦ ነበር።በመሆኑም የሚጠየቅበትም ክፍያ በጣም ጥቂትና የሰውን አቅም የተከተለ ነበር ።አሁን ግን በሙስና ቀለበት ውስጥ ገብቶ ብዙ ገንዘብ፣ ከመቶ ሽ ብር በላይ የሚጠየቅበት፣ ለደሃው መኖሪያ ሳይሆን አቅም ያለው እየገዛ የሚያከራየው ይዞታ (ኢንቨስትመንት) እየሆነ መጥቷል። በመጀመሪያው ወቅት ግን ከአራት እስከ አስራ አራት ሽ ብር ያለው ከፍሎ ቀሪውን በተራዘመ ብድር  የቤቱ ባለቤት የሚሆንበት ዕድል ነበረው።ዓላማው በመሰረቱ የሚነቀፍ አይደለም።የሰው ልጅ ቀርቶ እንስሳ መኖር ከማይገባው ደሳሳና ቁሻሻ መኖሪያ ጎጆ ወጥቶ የተሻለ ቤት ውስጥ እንዲኖር ማድረግ የሚመሰገን እርምጃ ነው።ሂደቱ እንዲቀጥል ማበረታታት ያስፈልጋል።ሆኖም ግን በቢሮክራሲው አመራር ውስጥ የተሰገሰጉ ጅቦች በጥቅም የሚቸረችሩት ሸቀጥ ሆኖ እንዳይቀር ለሕዝቡ የቆመ ሃይል ካለ ጉዳዩን ሊያስብበት ይገባል።የባንኮችም ሃላፊዎች ለቤት መግዣ የሚውለውን ብድር ለማግኘት የሚያስችለውን ቅድመ መጠይቅ የሚያሟሉትን ሰዎች በሆነ ባልሆነው ምክንያትና ጥቅማ ጥቅም ብድር እንዳያገኙ መከልከል በተጠቃሚውና በሚሰሩበት ድርጅቱ ላይ በደል መፈጸም ይሆናል።  በተጠቃሚውም ዙሪያ የሚታይ ጥፋት አለ።ይኸውም ይኖርበታል ተብሎ የተሰጠውን ዕድል በሽያጭ ወይም በኪራይ ለሌላ አሳልፎ በመስጠት ተመልሶ ወደ ነበረበት የቀበሌ ደሳሳ ቤት በመግባት የነበረው  ቁሻሻ ከባቢ ለውጥ እንዳያመጣ እንቅፋት ሆኗል። የሌላውን እድል በመዝጋት የተሰጠውን ዕድል ባግባቡ ሳይጠቀምበት ከቀረ ተመልሶ ቀበሌ ቤት የማይገባበት፣ለማከራየትና ለመሸጥ የማይችልበት ደንብ ወጥቶ ቢከበር የተሻለ ነው።

የእህል ዋጋ እየጨመረ እንጂ እየቀነሰ አልመጣም።1300 ብር የነበረው ጤፍ 1500 ሲሆን ተወደደ ይባላል፤ ተመልሶ ወደ ነበረበት ዋጋ ወደ 1300 ሲገባ አሁን ቀነሰ ተብሎ ይነገራል።በዚህ መልኩ ማውጣት የማይኖርበት ዕቃ ወይም እህል በተጠየቀው ዋጋ እንዲሸጥ ይደረጋል።ሌላው ብዙሃን ስራ አጥ ቀርቶ የአማካኝ የወር ገቢው ከ250 ብር የማይበልጥ ሰራተኛ ዕብረተሰብ እንዴት አድርጎ በብዙ መቶና ሽ ብር የሚጠራ ዋጋ ያለውን ለመግዛትና ለመጠቀም ይችላል?በጤፉ ዙሪያ ያለውን አነሳሁ እንጂ በሌላውም ቢሆን ከዚያ የተለዩና የተሻለ ሁኔታ የለም።ሁሉም ነገር ከአምናው ቢያንስ ቢያንስ ከ50%-100% ከዛም በላይ ጨምሯል።

እንኳንስ ዘንቦብሽ እንደውም ጤዛ ነሽ እንደሚባለው ፣እንኳንስ በችግር ላይ ችግር ተደራርቦ ይቅርና በነበረውም የታወቀ ችግር ሳቢያ ስራ አግኝቶ ለመስራት የቻለው ሕዝብ በተለይም ወጣት በጣም ጥቂቱ ነው።ቤተሰቡ የኪስ ገንዘብ ሊሰጠው የሚችለው ወይም በውጭ አገር ከሚኖር ዘመዱ ገንዘብ የሚላክለት ጊዜውን የሚያሳልፈው በየቦታው በብዛት በተከፈቱት ካፌና ሻይ ቤቶች ከቦ በማውራት ወይም ጋዜጣ በማንበብ ነው። አንዳንዱም  የሚሰራው ሲያጣ በሰውነቱና በምግባሩ ላይ ጉዳትና ስብራት በሚያመጡ ተግባሮች፣ጫት በመቃም፣ሀሺሽ በማጨስ፣አልኮል በመውሰድ ተግባር ላይ ተሰማርቶ ፣ከሰውነት ወጥቶ፣ምግባረ ቢስ ሆኖ ሲያዩት ያሳዝናል።ሌላው ደግሞ ቅጥ አምባሩ ዞሮበት ከሰፈሩ ሳይወጣ የቤቱን አጥር በር ተደግፎ ወጭ ወራጁን ሲታዘብ አልፎ አልፎም  ሲለክፍና በቤቱ ገባ ወጣ እያለ የሚውለው፣ በቤቱ ዲሽና ቴሌቪዥን ካለው(ኤሌክትሪክ በሚኖርበት ጊዜ)ተጎልቶ ዓይኑንና ጆሮውን ሲጎዳ  የሚውለው  ቁጥሩ ትንሽ አይደለም።ይህ ሁሉ ወጣት ሌላው ቢቀር ተሰባስቦ የሚውልበት፣ የሚያነብበት፣ስፖርት የሚጫወትበት፣ሙያ የሚቀስምበት ዕድልና ቦታ ቢፈጠርለት ለወጣቱም ለሕብረተሰቡም የሚሰጠው ጥቅም ከፍተኛ ነው።ለዚህም ነው የወጣቶች ማዕከል( ሴንተር) አስፈላጊ ነው የምለው።በዚያም ዙሪያ የምሯሯጠው።

በችግር የተነሳ ሴቶች ወጣቶችም ለብዙ አደጋና በሽታ ተጋልጠዋል።በየአረብ አገሩ ተሰደው የመከራ ኑሮ የሚገፉትንና ሕይወታቸውን ያጡትን የአካልና የአእምሮ ጉዳት ደርሶባቸው የቤተሰብ ሸክም የሆኑትን ቤት ይቁጠራቸው ከማለት በስተቀር ይህን ያህል ናቸው ብሎ ለመናገር አይቻልም።በውጭ አገር በሚኖሩበት ጊዜ ለመብታቸውና ለደህንነታቸው የሚቆምና የሚከራከር የመንግስትም ሆነ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት አለመኖሩ ያሳዝናል።

## በቢሮክራሲው ዙሪያ

በዚህ ከባቢ የሚካሄደው ችግር በተደጋጋሚ በመገለጹ የማያውቅ እንግዳ ይኖራል ብዬ አልገምትም። ሆኖም ግን እኔ እራሴ በመንገዱ በማለፍ ያየሁትንና የታዘብኩትን እንደማስረጃ በማቅረብ ለማሳየት እወዳለሁ።

ከላይ እንደገለጽኩት አዲስ አበባ ስገባ የነበረኝ የአምስት ዓመት ቪዛና የመኖሪያ ፈቃድ(ቢጫ ካርድ) በመቃጠሉ በግዴታ ጊዜያዊ የመግቢያ ፍቃድ ማውጣት ነበረብኝ፤ እሱንም ሃያ ዶላር በመክፈል ለመግዛት ችያለሁ።በተደጋጋሚ እመላለሳለሁ ብዬ ስለማስብ የነበረኝን የረጂም ጊዜ ፈቃድ ለማሳደስ ጉዳዩ ወደ ሚመለከተው መስሪያ ቤት ማለትም ኢሚግሬሽን ቢሮ መሄድ ነበረብኝ።ለመግባት ችግር አልገጠመኝም።አስተናጋጆቹ በትህትና ተቀብለው መሄድ ወደሚኖርብኝ ክፍል መሩኝ።በተባለው ክፍል ቀርቤ ለጥያቄዬ መሞላት የሚያስፈልገው ፎርም ተሰጠኝ።ያንን ሞልቸ ስጨርስ ወደ ማቀርብበት ሌላ ክፍል ይገፔ ገባሁ፣እዛ ተቀምጠው የነበሩት ባለስልጣን ፈርመዉበት ወደሚቀጥለው ክፍል እንድሄድ ተነገረኝ።እዛም የነበሩት ባለስልጣን ፈርመውበት ወደሌላ ቁጥር ቢሮ መሩኝ ፤እዛም በባለስልጣኑ ተፈርሞበት ወደ መዝገብ ቤት ተመራሁ።የመዝገብ ቤቱ ሰራተኛ አንድ ግማሽ ሰዓት እንደሚፈጅና መጠበቅ እንደሚኖርብኝ ገለጹልኝ። እንደተባልኩት በእንግዳ መቀመጫው ሰፊ አዳራሽ ተራዬን በመጠበቅ ዙሪያ ገጠሙን መታዘብ ጀመርኩ።ብዙ ወጣት ሴቶች ወደ ውጭ አገር በተለይም ወደ አረብ አገር ለመሄድ የሚያስችላቸውን ፈቃድና ፓስፖርት ለማውጣት ደጅ እንደሚጠኑ ተገነዘብኩ።ከአዳራሹም በመውጣት የግቢውን ዙሪያ በሰልፍ ሞልተው ተራቸውን የሚጠባበቁትን ተመለከትኩ።የጠያቂው ብዛት እየጨመረ ሰልፉ እየተለጠጠ ሲሄድ እንጂ እየቀነሰ ሲሄድ አላየሁም።ከድካምና ከመሰልቸት የተነሳ ግድግዳ ተደግፎ የቆመው፣ በያለበት መሬት ላይ የሚቀመጠው፣ጥላ እየፈለገ በበረንዳውና በየዛፉ ስር የሚጠለለው ብዙ ነው። ጧት በማለዳ ተራ ለመያዝ ከቤቱ ወጥቶ የዋለ በመሆኑ ሁሉም ደክሞታል።ምናልባትም ቁርስ ሳይበላ የወጣ ይኖር ይሆናል። የማስተናገዱ ሂደት በጣም ዝግምተኛ ነው።

የተሰጠኝ የጊዜ ገደብ በመቃረቡ ውጤቱን ለመጠየቅ ወደ መዝገብ ቤቱ ሄድኩኝ።ያገኘሁት መልስ ግን “ከሚኖሩበት አገር መዝገብዎ አልመጣም ስለዚህ ወደ ቁጥር... ተመልሰው ሄደው ይጠይቁ” ተባልኩ።ወደተባልኩት ቢሮ ስሄድ ባለስልጣኑ ለምሳ መውጣታቸው ተነገረኝ።ተመልሰው የሚገቡት በሰባት ሰዓት ተኩል ነው፣ማለትም ከአንድ ሰዓት በኂላ መሆኑ ነው።ሄጄ ተመልሼ ከምመጣ እዛው በግቢው ውስጥ የሚታየውን ትርዒት መመልከቱን መረጥኩ።አሁንም በሰልፍ ተራቸውን የሚጠብቁት ባለጉዳዮች በነበረው ሁኔታ ላይ ናቸው፤ጉዳዩን ጨርሶ የሄደ ያለ አይመስልም።በጣም የሚያሳዝነው ነገር የመጡበት ጉዳይ ቢታሰብበት ኖሮ ከሚኖሩበት የቀበሌ ጽ/ቤት የሚያልፍ አልነበረም።ያ ቢሆን ደግሞ በአንድ መስሪያ ቤት የሚያስከትለው የስራ ጫናና የባለጉዳይ መንገላታት ባልተፈጠረም ነበር።

ባለስልጣኑ ይገባሉ በተባለበት ሰዓት ሳይሆን ግማሽ ሰዓት አሳልፈው መጡ።ጉዳዩን ገለጽኩላቸው።በወረቀቱ ላይ ፈረሙና ወደሚመለከተው ቢሮ ቁጥር መሩኝ፤እዛም ተፈርሞበት ወደሌላ ቢሮ ተላኩኝ እዛም የተቀመጡት ባለስልጣን ፈርመውበት ለሚቀጥለው ባለተራ ባለስልጣን ቢሮ ላኩኝ።እዛ የተመደቡት ሰራተኞች መዝገቡ ከጠፋ የሚመለከተውን ቤልጅዬም የሚገኘውን ኤምባሲ በፋክስ እንዲልክልን እንጠይቃለን፤መልሱ እንደመጣ ስልክ እንደውላለን ብለውኝ የሞባይል ስልክ ቁጥር ሰጥቼ ከዓምስት ሰዓትና የሰባት ባለስልጣኖች ቢሮ መላጋት በኂላ ግቢውን ጥዬ ወጣሁ።ግቢውን ከመውጣቴ በፊት ዘወር ብየ ወደ ባለጉዳዮቹ የወረፋ ሰልፍ ስመለከት ያው ነው፣አልቀነሰም።በልቤ ብርታቱን ይስጣችሁ ብዬ መንገዴን ቀጠልኩ።

በዚህ አጋጣሚ የታዘብኩት ሌላው ነገር ቢኖር በገባሁባቸው ሰባት የሚሆኑ ቢሮዎች ውስጥ በትልቁ ጥቁር ወንበር ላይ ከተቀመጡት አላፊዎች/ባለስልጣኖች/መካከል አራቱ የአንድ ከባቢና ብሄር ተወላጆች ማለትም ትግራዮች መሆናቸውን ነው።እዚህ ላይ ለምን የትግራይ ተወላጆች በስልጣን ላይ ተቀመጡ ማለቴ አይደለም፤ቦታው የሚጠይቀውን ካሟሉና ችሎታ ከፈቀደላቸው፣በጎሳና ድርጅታዊ ስበት ሳይሆን ለስራው ከሌላው ዜጋ ተሽለው ከተገኙ ሙሉ ለሙሉ መስሪያ ቤቱን ቢቆጣጠሩት ተቃውሞ የለኝም።ነገር ግን ሹመቱና ምደባው ድርጅታዊና ወገናዊ ብሎም የጎሳ ጥቅምንና የበላይነትን የሚያንጸባርቅ፣ ሌላውን ያገሪቱን ዜጋ መብትና የስራ ድርሻ የሚገፍ ከሆነ በቅጡ ሊኮነንና ሊወገዝ ይገባዋል።መካድ የሌለበት ነገር በአለፉት አስራ ሰባት ዓመቶች በስልጣን ላይ የተቀመጠው ሃይል የኔ ናቸው የሚላቸውንና የሚተማመንባቸውን በልዩ ልዩ መስኮች ማስተማሩና ማሰልጠኑን ነው።በመጀመሪያው የስልጣን ዘመን የአስተዳደሩን ቦታ ይዘው የነበሩት የጦር ሜዳ ሰዎች በልዩ ልዩ መንገድ እየሰለጠኑ ወይም በሰለጠኑት እየተተኩ ወደ ሌላ ስራ ተመድበዋል።በዚህ ላይ የተማረው የሌላው ብሄር ተወላጅ በሆነ ባልሆነው ምክንያት አገር እየለቀቀ ሲወጣ በአስተዳደሩ የረኩትና ድርጅታዊም ሆነ ክልላዊ ስሜት ያስተሳሰራቸው ሰዎች አለተፎካካሪ የሃላፊነቱን ቦታ ለመውሰድ እድልና አጋጣሚ ያገኛሉ።የዚህ አይነቱ አሰራር ዛሬ የተጀመረ ሳይሆን በቀደሙትም ስርዓቶች የተለመደ ነበር፤በአንድ

መስሪያ ቤት ውስጥ የሃላፊነት ቦታ ይዘው የነበሩት ባለስልጣኖች ሰራተኛ  የሚጠቀጥቁት በከባቢ ስሜትና በጥቅማ ጥቅም አኳያ እንደነበር በዚያ ያለፉ፣የተጎዱና የተጠቀሙት ያውቁታል።ለለውጡም ጥሪ አንዱ ምክንያት የነበረው የዚህ አይነቱ አሰራርና ልማድ ነበር።አለመታደል ሆኖ መንግስታት ሲለዋወጡ እንደ ባሕል ተጠብቆ ኖሯል። ወደፊትም ከዚህ አይነቱ አሰራር ለመገላገል የሕዝቡን መብት ከስልጣኑና ከጥቅሙ በላይ የሚያይ፣ሁሉንም በእኩልነት የሚመለከት መንግስትና ስርዓት ሲመጣ ነው።

ይህ አይነቱ አሰራር የተለመደ ባህል እንዳይሆን፣የስራና ያላፊነት ቦታ ስልጣን ለያዘ ሃይል ደጋፊዎችና የድርጅት አባላት የሚሰጥ ወይም የሚያዝ ድርጅታዊ ንብረት ሆኖ እንዳይቀር ወገናዊነትንና ኋላ ቀር ጎሳዊ አመለካከትን የሚያንጸባርቅ ፖለቲካ ጭራሽ መጥፋት ይኖርበታል።በቦታው አገር አቀፍ አመለካከትን የሚያዳብርና የሚያጎለብት የፖለቲካ ባህል መተካት ለእኩልነት፣ ለሰላምና ለድገት መሰረት ነው።

እዚህ ላይ የአሁኑ የአሜሪካን ፕሬዚደንት ባራክ ኦባማ “ከአባቴ ህልሞች/ራዕዮች/from the dreams of my father”በሚለው መጽሀፋቸው ውስጥ በገጽ አስራ አንድ ላይ ያሰፈሩትን ምክር ለመጥቀስ እወዳለሁ።

“ .... I know that the hardening of Lines, the embrace of fundamentalism and tribe, dooms us all.”ሲተረጎም ”የመስመር አጥባቂነትና አክራሪነት እንዲሁም ዘረኝነት ሁላችንንም ገደል እንደሚከተንና እንደሚጎዳን አውቃለሁ”  በማለት በዚያ ዙሪያ ተሰልፈው የጥፋት ከበሮ የሚደልቁትን መክሮ ለመመለስ ሞክረዋል።

ወደ አልጨረስኩት የኢሚግሬሽን ጉዳይ ልመልሳችሁና

በተባልኩት መሰረት ስልክ ይደወልልኝ ይሆናል በማለት ለቀናቶች ጠብቄ ምንም ባለመስማቴ ከአምስት ቀናት በኋላ ተመልሽ በመሄድ ብጠይቅ  ፋክስ ተልኮ ምንም አይነት መልስ እንዳልመጣ ተነገረኝ።ሁኔታውን ለሚመለከታቸው የበላይ ባለስልጣን ባመለከትም እሳቸውም ዳግመኛ ፋክስ ልኮ ከመጠየቅ በቀር ምንም ማድረግ እንደማይቻል ገልጸውልኝ ፣ጸሃፊያቸውን በአስቸኳይ ዳግመኛ ፋክስ እንድታደርግ አዘው መልስ ከመጣ እንደሚደወልልኝ ገልጸው አሰናበቱኝ።ይደወላል የተባለው ስልክ ሳይደወልልኝ የምመለስበት ቀን እየተቃረበ በመምጣቱ ተስፋ ቆርጬ ጉዳዩን ባለሁበት ለመከታተል ወስኘ ተመለስኩ።

ከመጣሁ በኋላ ቤልጅየም የሚገኘውን የኢትዮጵያ ኤምባሲ ብጠይቅ፣መዝገቡ ከሆላንድ አልተላለፈልንም ብለው ነገሩኝ።ሆላንድ ውስጥ የነበረው ቆንስል ቢሮውን ሲዘጋ ስርዓት የተከተለ አልነበረም።እንኳንስ መዝገብ ሊረካከብ ቀርቶ የተሰቀለ ባንዲራ ሳይወርድ፣የስምንት ወር ቤት ኪራይ ሳይከፈል፣የሰራተኞች ደመወዝ ና ስራ መፈለጊያ ካሳ ሳይሰጣቸው ሁሉም በያቅጣጫው፣በስደትና በዝውውር የተበተነበት ሁኔታ ነበር።ከጠቅላላው ሰራተኛ የመቀየር እድል ያገኙት ሁለት ሰዎች ብቻ ናቸው።እነሱም የድርጅት ሰዎች በመሆናቸው ነው ይባላል።ጥቂቶቹ የከባቢው ቅጥረኞች ከጊዜ በኋላ በክርክር ያልተከፈለ ደመወዛቸውና የመሰናበቻ አበል ማግኘታቸውን ሰምቻለሁ።

እንደ አሰራሩ ቢሆንማ ኖሮ የትም ይሁን የትም በመንግስት ባለስልጣን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ካርኒ ተቆርጦበት የተሰጠ መታወቂያ፣የባለስልጣኑ ተወካይ ወይም ወካዩ ባለስልጣን በሚኖርበት አገርና አካባቢ ማደስና መለወጥ በተገባ ነበር።በዚህም አሰራር የተፈጸመላቸው እንዳሉ በውስጠ አዋቂ ልሰማ ችያለሁ።እኔን የገጠመኝ ግን በዚህ ምክንያት ነው ብዬ ለመናገር እርግጠኛ ባልሆንም፣ በግምቴ መንግስት ባለበት የውጭ ምንዛሪ ችግር የተነሳ በውጭ አገር የሚኖሩት የኔ ቢጤዎች ጉዳያቸውን ለማስፈጸም መከፈል የሚገባውን ክፍያ በዛው አገር ገንዘብ በተለይም በፓውንድ፣ በዶላርና ኢሮ እንዲሆን በማስፈለጉ በወጣው መመሪያ ይመስለኛል። በተገቢው ቦታ ላይ ከዋለ በዚህ ቅዋሜ የለኝም።ጥያቄዬን ለማስፈጸም የግድ አዲስ መዝገብ መከፈት ይኖርበታል ስለተባልኩ፣ እኔነቴን የሚገልጽ ማስረጃ(የልደት፣የጋብቻ፣አሮጌና አዲስ ፓስፖርት)ይዤ እንድቀርብ ስለተነገረኝ ሲሟላልኝ ብቅ ለማለት አስቤአለሁ።

የሚያሳዝነው ነገር  አንድ ባለስልጣን በአንድ ቢሮ ውስጥ ሊፈጽመው የሚገባው ነገር በማያስፈልግ የቢሮክራሲ ሰንሰለት ተተብትቦ ማልፋቱ፣ ለሌላ ተግባር ሊውል የሚችለውን ጊዜና ጉልበት በከንቱ ማፍሰሱ ነው። የቢሮክራሲው መስፋት ለሰዎች የስራ  እድል ለመፍጠር ታስቦ ከሆነ በባለጉዳይ ላይ ጉዳት በማያስከትልበት መልኩ ቢሆን ይመረጣል።በዚህ መስሪያ ቤት ውስጥ አንዳንዶቹ ባለስልጣኖች የሚያሳዩት ትህትናና አቀባበል፣ምንም እንኳን ጉዳዩን ባይፈጽሙም የተሻለ ነው።አንዳንዶቹም ሳያናግሩ ፊታቸውን ከስክሰው ፣በቀረበላቸው ወረቀት ላይ ብቻ የተገደዱ ያህል እያማጡ የሚፈርሙም አጋጥመውኛል።

በዚህ አጋጣሚ በአገሪቱ ውስጥ በልዩ ልዩ ዘርፍ የኢንቨስትመንት ስራ ለማካሄድ የመግቢያና የመውጫ/የመኖሪያ/ ፈቃድ ለመጠየቅ በቦታው ተገኝተው የነበሩትን ብዙ የአረብ፣የቱርክና አንዳንድ አውሮፓውያንን ለመመልከት ችያለሁ፤እነሱ የሚቀርቡት በጉዳይ አስፈጻሚ እርዳታ ስለሆነ በፍጥነት ይስተናገዳሉ።ይህ በመሆኑ በአገሪቱ ወይም በመስሪያ ቤቱ ላይ ጥቁር አመለካከት አይኖራቸውም ብዬ እገምታለሁ።ካላቸው ግን የገጠማቸውን የሚያውቁት እራሳቸው ስለሆኑ ዝርዝሩን ለነሱ ትቸዋለሁ።

ሙስና (ጉቦ)

የአንድ አገር ሕዝብ ማግኘት የሚገባው ነገር በሕግ ካልተረጋገጠ፤መብትና ግዴታውን እንዲገነዘብና እንዲረዳ ካልተደረገ፣በዜግነቱ ወይም በሰውነቱ ማግኘት የሚገባው ሁሉ የመንግስትና የባለስልጣኖች በጎ አድራጎትና ችሮታ ተደርጎ ከተቆጠረ ፣የሚፈልገውን ለማግኘት የፈቃጆን በጎ አስተያየትና ውሳኔ ለማግኘት የሚጠየቀውን ለማድረግ ይገደዳል።በ"ደሃ" አገሮች ለድህነታቸው ምክንያት የሆነው ዋናው ነገር ሕዝቦች የመብታቸው ባለቤት አለመሆናቸው ነው።ይህ የመብት አለመታወቅና አለመከበር ደግሞ ለስልጣን ብልግናና ሙስና መፈጠር ዋናው ምክንያት ይሆናል።

ግልጽና ጥርት ያለ መመሪያ ከለለ፣ድብስብስ ያለና የሚያሻማ ደንብና ህግ በባለስልጣን ፍላጎትና ምርጫ ለሚያልፍ ውሳኔ ይዳርጋል።ይህንን የባለስልጣን በጎ ውሳኔ ለማግኘት ደግሞ ባለስልጣኑን የሚማርክ ነገር ይዞ መቅረብ ግዴታ ነው።በአብዛኛው ጊዜ ያበጠ ቦርሳ ይዞ መቅረብ ይጠይቃል።በሌላውም መንገድ ባለጉዳይ አነስታይ ከሆነች መለገስ የሚኖርባት ተጨማሪ ስጦታ ይኖራል፣እራሷን አሳልፋ እንድትሰጥ ትገደዳለች።በዚህ መልክ የሚጠየቀውን ሳያሟላ ማግኘት የሚገባውን እያጣና እየተነጠቀ የሚያለቅሰው ተበዳይ ቁጥር ይህ ነው አይባልም።

በቦታና በቤት፣በስራና በትምህርት ዕድል፣በባንክ ብድር፣በግብር ክፍያ...ወዘተ ዙሪያ ሙስና በግልጽ የሚራመድበት መድረክ ነው።ይህንን የሚያመላክቱ ምሳሌዎች ለመጠቆም እወዳለሁ።

ባለው የውጭ ምንዛሬ እጥረት ባለድርጅቶችና ነጋዴዎች ከውጭ አገር ተገዝቶ የሚገባ ለስራ የሚያስፈልግ መሳሪያና ጥሬ ነገር እጥረት ገጥሟቸዋል።በባንክ ማግኘት የሚገባቸው ሌተር ኦፍ ክሬዲት በቀላሉ አይገኝም፣ባንኩም የውጭ አገር ምንዛሬ ተቸግሯል።ቢኖረውም በጣም የተወሰነ ነው።ይህንን የተወሰነ የውጭ ምንዛሪ በካዝናቸው የያዙ የባንክ ስራ መሪዎች (አስተዳዳሪዎች) የራሳቸውን ጥቅም ሲያራምዱበት ይሰማል፤ይኸውም በየአንዳንዷ የአሜሪካ ብር ምንዛሪ ሶስት የኢትዮጵያ ብር ለግላቸው እንዲከፈላቸው ጠያቂውን በማስገደድ ነው።የአስር ሽ ዶላር L C(ሌተር ኦፈ ክሬዲት)ለማሰራት ሰላሳ ሽህ የኢትዮጵያ ብር መክፈል ግዴታ ነው ማለት ነው።

በሌላው ደግሞ ቦታና ቤትን በሚመለከተው ዙሪያ፡-በመንግስት መመሪያ መሰረት የዱሮ የቦታ ካርታ ያላቸው ባለመሬቶች ከሚመለከተው መስሪያ ቤት አቅርበው በአዲስ ካርታ እንዲለውጡ አስገዳጅ ትእዛዝ ወጥቷል።ይህንን ደንብ በማክበር ወደተባለው መስሪያ ቤት ካርታ ክፍል ሲኬድ የሚገጥመው ነገር ሌላ ነው።ነባሩ ካርታ ይወሰድና ለአዲሱ ቀጠሮ ይሰጣል፣በቀጠሮው ሲኬድ እንግዳና ያልጠበቁት ነገር ይፈጠራል።የተወሰደው ካርታ የት እንደገባ ይጠፋል፣ከነጭራሹ አላመጣህም ተብሎ በባለቤቱ ላይ ክህደትና ዘለፋ ይወርድበታል።ቢወጣ ቢወርድ ልፋት ብቻ ይሆናል።በሰው በሰው ችግሩ የሚፈታበት ብቸኛ መንገድ ገንዘብ(ሙስና) ይሆንና እንደቦታው ስፋት ከሰላሳ ሽ ብር በላይ ተከፍሎ በነጻ ማግኘት የሚገባውን የባለቤትነት ማስረጃ ካርታ ከድካምና ከብስጭት ጋር ገዝቶ መመለስ የተለመደ ሆኗል። በተጨማሪም በካርታህ ውስጥ አልአግባብ ትርፍ ቦታ ጨምረሃል ተብሎ ለዛ ማካካሻ ለባለስልጣኑ ጉርሻ እንዲሰጥ የሚገደደው ብዙ ነው።

ሌላው አሳዛኝ ነገር ደግሞ በግልም ሆነ በቡድን በአንድ ከባቢ የህክምናም ይሁን የማምረቻ ተቋም ለመገንባት በሚፈልጉ ባለሃብቶች የመሬትና የግንባታ ፈቃድ ጥያቄ ሲቀርብ የከባቢው ባለስልጣኖች የተወሰነ ባለቤትነት ድርሻ(partnership) ወይም ከፍተኛ ገንዘብ እንዲሰጣቸው መጠየቅና ማስገደድ የተለመደ ሆኗል።በዚያ ተስማምቶ ያሉትን ያላደረገ ያሰበውንና የሚፈልገውን አያገኝም፤ለህብረተሰቡ ምንም አይነት ጥቅም ይኑረው ባለስልጣኖች የሚጠይቁት ካልተሟላ በተግባር አይገለጽም።የግድ የጥቅም ውል በዝግ ቢሮ መፈጸም አለበት።እንግዲህ ለዚህ ሁሉ በደል ተጠያቂው ማን ነው?

ክልሎች ለሚያካሂዱት የግንባታና የልማት እንቅስቃሴ የሚያስፈልጋቸውን መሳሪያና ዕቃ በቅድሚያና በሰፊው እንዲያገኙ የሚያበቃቸው የመንግስት ፈቃድ አላቸው።ይህንን ዕድልና መብት በክልሉ የስልጣን ሰንሰለት ውስጥ የተሰገሰጉ ግለሰቦች አላግባብ መጠቀማቸው ይወራል።ለክልሉ የተመደበው በተለይም ሲሚንቶና ፌሮ/ብረታ

ብረት/ከሚያስፈልገው በላይ በመጠየቅ የተረከቡት በጥቅም ላይ ይውላል ከተባለው ቦታ ሳይደርስ ተዟዙሮ ይቸበቸባል።በዚህ የአየር ባየር ገበያ ተጠቃሚ ቢኖር ደላላና ባለስልጣኖቹ ናቸው።

## በፖለቲካው ዙሪያ

በዚህ መስክ ከበፊቱ የተለወጠ አዲስ የፖለቲካ ሰልፍና የጎላ የተቃዋሚ እንቅስቃሴ አይታይም።ጋቢናውን ይዞ በዚህ በዚያ እያለ በፈለገበት አቅጣጫ የሚያሽከረክረው በስልጣን ላይ ያለው ነጠላም ጥምርም የመሆን መልክ የሚያሳየው የፖለቲካ ድርጅት ነው።ተቃዋሚ ነን የሚሉት አብዛኞቹ በተፈቀደላቸው የጨዋታ ሜዳ ከመንቀሳቀስ ውጭ የተለየና ሕዝቡን ለለውጥ የሚያበቃ ስራ ሲያካሂዱ አይታይም።እንኳንስ መንግስትን ለመለወጥ በሚያስችለው ተግባርና ትግል ላይ ሊውሉ ቀርቶ እንደነሱ በተቃዋሚነት በፖለቲካ ድርጅት ስራ ተሰማርተው ከመንግስት ጋር በተፈጠረው ግጭት እስር ቤት የሚማቅቁትን ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳን ለማስፈታት ህጋዊም ሆነ ፖለቲካዊ ጥረት ሲያደርጉ አይታይም። ታዲያ እንደዚህ ከሆኑት ተቃዋሚ ነን ከሚሉ ድርጅቶች ምን ይጠበቃል? ለመሰል ድርጅት አባላት መብት ለመቆም ያልደፈሩ ለመላ ሕዝብ ጥቅም ይቆማሉ ብሎ ማሰብ ሞኝነት አይሆንም?

አንዳንዶቹም ይባስ ብለው ሕዝቡን አስጨንቆና ወጥሮ የያዘውን እለታዊ ችግር፣አገሪቱ የተደቀነችበትን አደጋ ትኩረት ሳይሰጡ በባንዲራ ቀለም ሲጨቃጨቁና አቋም ሲወስዱ ይታያል።ለመሆኑ በሚጠይቁት ባንዲራ ስር አልነበረም እንዴ ሕዝብ የተራበው፣መብቱን የተገፈፈው፣የተሰደደው? በዘመነ ዘውድና በፋሽስቱ ደርግ ወቅት የተካሄደው ግፍ በዛው ባንዲራ ጥላ ስር መሆኑን ማን ይረሳል? ቁም ነገሩ የባንዲራው ቀለም ሳይሆን ስርዓቱ ነው።አሁንም ሆነ ወደፊትም የባንዲራው ቀለምና የሚለጠፍበት መፈክርም ሆነ ስዕልና ጌጥ ለሃቀኛ አስተዳደርና ለዲሞክራሲ ስርዓት ዋስትና አይሰጥም።

የባንዲራ ጥያቄ በብዙሃኑ ፍላጎትና ምርጫ፣ድምጽ ሰጥቶበት የሚወሰን እንጂ ስልጣን ላይ የወጣ ሁሉ እንደፈለገ መልክ እየመረጠ የሚሻውን ምልክት የሚለጥፍበት ሰሌዳ አይደለም።ያማ ከሆነ ስልጣን ላይ በወጡ በወረዱ ቁጥር ባንዲራ ሲቀይሩ መኖር ይሆናል። እንደ ሕዝቡ የመከራ ተሸካሚ ሆኖ የኖረው ባንዲራ ከአገርና ከሕዝብ አርማነት ይልቅ የመንግስታቱ መልክና ስሜት መግለጫ ማለያ(ትጥቅ) ሆኖ ኖሯል።በንጉሱ ጊዜ አውሬ (አንበሳ) በፋሽስቱ ደርግ ጊዜ ማጭድና መዶሻ፣በአሁኑ መንግስት ጊዜ ደግሞ ዘር ይወክላል የሚል ኮከብና ጭረት ያለው አርማ ተሸክሞ እንዲውለበለብ ተገዷል።በልዩ ልዩ ጊዜ የተነሱ የፖለቲካ ሃይሎች መጫወቻ የሆነው አርማ ለአንዱም ለሁሉም የሕዝቡን ፍላጎትና ስሜታ የሚያንጸባርቅ መሆን ይኖርበታል። የአሁኑ ባንዲራ ላይ የተለጠፈው ኮከብና ጭረት የብሄር ብሄራትን መብት የሚያንጸባርቅ ነው ተብሎ ብዙ ፕሮፓጋንዳ ስለተሰራበት፣ያንን ተቀብሎ የሚያምነውን ዜጋ ወደ ትክክለኛው አመለካከት ለመለወጥ በታሪካዊ ጥናት ላይ የተመሰረተ ሰፊ ዘመቻ ያስፈልጋል፤አለበለዚያ ግን ሌላ ትርጉም ይይዝና የሚፈራውን የህዝቦችን አለመግባባትና የርስ በርስ ግጭት ይጋብዛል።

በስልጣን ላይ ያለው የኢህአዴግ መንግስት ሕዝቡን ለመያዝ የማያደርገው ጥረት የለም።ፎረም የሚባል ፈሊጥ ተፈጥሮ ሕዝብ ድጋፉን የሚያንጸባርቅበት መድረክ በአገር አቀፍ ደረጃ ተከፍቷል።በተለይም በአዲስ አበባ ከተማ በሳምንት ውስጥ አንድ ወይም ሁለት ጊዜ ስብሰባ ይካሄዳል።በዚህ ስብሰባ ላይ የሚካፈል ተራ ተሳታፊ ሰው ከሰላሳ እስከ አምሳ ብር የሚደርስ የቀን አበል ሲከፈለው ምግብም ይቀርብለታል።አጋጣሚውን ለመጠቀም ሁሉም ይሽቀዳደማል።አብዛኛው በጉዳዩ አምኖበት ሳይሆን ለጥቅሚ ሲል ነው።"እኔ ምን ቸገረኝ እሰበሰባለሁ፤የሚባለውን በአንዱ ጆሮዬ አስገብቼ በሌላው አወጣለሁ፣ደግሞም የሚሰጠኝ ገንዘብና ምግብ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንጂ የወያኔ አይደለ....ወዘተ " እያለ የሚለው ቁጥሩ ቀላል አይደለም።አይምሮና ልብን አሳምኖ ለመግዛት ሳይቻል በሆድ መግዛትና ማሳመን አይቻልም፤ቢቻልም ለጊዜው ነው፤ዘላቂነት የለውም።ለዚህም ነው ብዙሃኑ "ልቤን ለኔ ሆዴን ለወያኔ" የሚለው።አዎ! የሚተማመንበት ሌላ ሀቀኛ ድርጅት ስለሌለ ልቡን አሳልፎ አይሰጥም።በዚህ ላይ የጆሮ ጠቢውና ያድር ባዩ ቁጥር አንድ ላንድ ነው ስለሚባል መተማመን ጠፍቷል።እርግጥ ነው ኑሮ ሲከብድና ችግር ሲበዛ የዚህ አይነቱ ጸባይ መንጸባረቅ የማይቀር ነገር ነው።ጥንካሬ ማለት ይህንን ፈተና ለማለፍ ደፍሮ መውጣት፣ አንድነት መፍጠርና መተማመን ለጥቅም ሌላውን አሳልፎ አለመስጠት ማለት ነው።ፍርሃትና እራስ ወዳድነት የማታ ማታ ለውድቀት ይዳርጋል። "አለአግባብ የበሉት በሶ ይወጣል ደም ጎርሶ ይባላል"የኋላ ኋላ ለከፋ ለህሊና ቁስል ይዳርጋል።።በደርግና ከዛ በፊት የነበረውን እያሰቡ ተመሳሳይ ጉድጓድ ውስጥ ላለመግባት መጠንቀቁ ብልህነት ነው።ከታሪክና ከሕሊና ወቀሳ ያድናል።

በምርጫ ቦርድ መግለጫ መሰረት ከዘጠኝ ወር በኋላ ለሚካሄደው አገር አቀፍ ምርጫ እስከአሁን ድረስ ዘጠና አንድ የሚሆኑ ድርጅቶች የተመዘገቡ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል። ይህ መግለጫ በውጭ አገርና የመንግስት እውቅናና ፈቃድ ሳይኖራቸው የሚንቀሳቀሱትን በአስርታት የሚቆጠሩትን አይጨምርም፤በሚመጣውም ዘጠኝ ወር በየቀኑ ወይም በየሳምንቱ እንደ ዶሮ የሚፈለፈሉትን አያጠቃልልም።የተያዘው ፈሊጥ ፣በፖለቲካ ድርጅት ስም እንደ ሱቅ ፈቃድ እያወጡ ወሬ መቸርቸር ሆኗል።

በጣም የሚገርም ነው፤ልዩነት እየጠበበ ይሂድ፤ የድርጅቶች መብዛት ችግሩን ውስብስብና ሕዝቡን ይከፋፍላል እየተባለ በሚነገርበት ወቅት እንዲህ አይነቱ የድርጅቶች ፋብሪካ መታየቱ ያሳዝናል።በአገሪቱ አሉ ተብለው ከሚገመቱት ጎሳና ብሄረሰቦች ቁጥር የድርጅቱ ቁጥር በልጧል።በዚህ ግርግር ተጠቃሚው ስልጣን ላይ የተቀመጠው ሃይል ነው።ሌላው በሆነ ባልሆነው ተከፋፍሎ ሲዳከር ተራ በተራ ነጣጥሎ እየመታ የስልጣን ዘመኑን ያራዝማል።

እነዚህ ከመቶ በላይ ሊሆኑ የሚችሉ "የፖለቲካ" ድርጅቶች አነሳሳቸው፣ምግባራቸውና አላማቸው ሲታይ የተለያዩ እሩይተ ዓለም/አይዲዮሎጂ/ ላይ የተመሰረተ መርሃ ግብር ያላቸው ሳይሆኑ፤ለስልጣና በጎሳና በከባቢ ትኩረት ላይ የተመሰረተ ጠባብ ዓላማ ያላቸው፣ተባብረው ሊሰሩ የማይችሉ፣ተከፋፍለው ሕዝቡን ይበልጥ ለመከፋፈል የሚጥሩ ናቸው።እንደው በደፈናው ከጅንጀሮ ቆንጆ ወይም ከእጅ አይሻል ዶማዎች ናቸው ማለቱ ይቀላል። ቢሻሉማ ኖሮ፣ለዲሞካራሲና ለሰብአዊ መብትማ ቢቆሙ ኖሮ፣እርስ በእርሳቸው መካከል መተባበር ቢኖርማ ኖሮ መሰል የድርጅት መሪ የሆኑት ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳና ሌሎቹም ተቃዋሚዎች በግፍ ሲታሰሩ በመተባበር ድምጻቸውን ያሰሙ ነበር።ያዩት ግን አንዱ ተፎካካሪያቸው የተወገደላቸው ወይም የተዳከመላቸው አድርገው ነው።ነግ በኔ መሆኑን ያወቁት አይመስልም።

ለአገሪቱ ሰላምና እድገት የድርጅት ጋጋታና ብዛት ሳይሆን የድርጅት ጥንካሬ፣ብስለትና አስተማማኝነት ነው።ድርጅቱ ለምንና ለማን ጥቅም እንደቆመ የሚያስረዳ ቁልጭ ያለ ፕሮግራም ይዞ መቅረቡና ሕዝብን ከኋላው ለማሰለፍ የሚችልበት የጥበብና የዕውቀት ባለቤት ሆኖ መገኘቱ ነው።በጥላቻና በአሉባልታ፣እንዲሁም በዘር በተበከለ አደረጃጀትና አሰራር አይደለም። በሀገሪቱ ውስጥ ከሁለት ወይም ግፋ ቢል ከሶስት የበለጠ የፖለቲካ ድርጅት አያስፈልግም። የሰራተኛውና የገበሬው ጥቅም የሚያስጠብቅ፣በተጻራሪውም ሌላውን ማለትም የከበርቴውንና ያሰሪውን መደብ የሚወክል (የግራና የቀኝ)ካስፈለገም ተጨማሪ የለዘብተኛ/ሊበራል / ፓርቲዎች ይበቃሉ።በዘር፣በክልልና በሃይማኖት ዙሪያ የሚነሱ ድርጅቶች ከጥቅሙ ጉዳታቸው ስለሚያመዝን በሕግ መከልከልና መታገድ ይኖርባቸዋል። የድርጅት ጋጋታ የዲሞክራሲ መብት መከበርንና መስፈንን አያመላክትም።

ከስልሳ እጅ በላይ ወጣት በሚኖርበት አገር ወጣቱ ወሳኝ የፖለቲካ ሚና ሊጫወት ይገባዋል።በተለይ በአለፉት ስርዓቶች ተጠቃሚና አደግዳጊ የነበረ፣አድር ባይ ግለሰብም ይሁን ቡድን የስልጣኑ ባለቤት እንዳይሆን መከላከል ተገቢ ነው።ያ ካልሆነ ግን የባህልና የፖለቲካ ለውጥ አይመጣም።ለውጡ የስም ብቻ ይሆናል።ለውጡ የጅራፍ ይሆናል።

መንግስት በሌላውም አቅጣጫ አባላት ለማብዛት በመስሪያ ቤትና በትምህርት ቤት ዘመቻውን አጧጡፏል።በስራው ለመቆየትና ትምህርት ሲጨርስ ስራ ለመያዝ የሚያበቃው መብትና ዋስትና ከዚሁ ጋር የተያያዘ በመሆኑ ተማሪና ሰራተኛው ሳይወዱ የሚቀበሉት ግዴታ እየሆነ መጥቷል።

ወጣቱን ለመያዝ የማይደረግ ሙከራ የለም።እረዳት የሌላቸው ችግረኛ ወጣቶች እየተደራጁ በከተማው መካከልና በከባቢያቸው በሚገኙ ዋና ዋና አውራ መንገድ ዳርና ዳር በሚገኙ የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች አነስተኛ ክፍያ እያስከፈሉ በገቢው እንዲተዳደሩ ፈቃድ ሰጥቷል።የፖለቲካ ተሳትፎን የማይጠይቅ የዜጋን ሰርቶ የመጠቀም መብት የሚያረጋግጥ ከሆነ የሚነቀፍ አይደለም።የታሪክን ገጽ ወደ ኋላ ገለጥ አድርገን ብንመለከት በደርግ ጊዜ ሕዝብ ማግኘት የሚኖርበትን መብት፣በቀበሌ ሱቅ ለመግዛት የሚፈልገውን እቃ፣ሊያገኝ የሚችለው "ለአብዮቱ ታማኝና ደጋፊ" መሆኑን ሲያረጋግጥ ነበር።አሁንስ ከዛ የተለዩ ነው? በምርጫ ዘጠና ሰባትም የሆነውን ማስታወስ ለብልህ ትምህርት ይሰጣል።መንግስትን ደግፎ የንብ ምልክት ካናቴራ ለብሶ እንዲወጣ የተገደደው በማግስቱ ካናቴራውን ገልብጦና አውልቆ በተቃዋሚነት መሰለፉን ማስታወስ ፣ሕዝብ ተገዶና በጥቅም ተይዞ የሚሰጠው ድጋፍ ዘላቂነት አለመኖሩን ያስገነዝባል። ለሚያስተማምን የሕዝብ ድጋፍ፣ ሕዝብ የሚሻውንና የሚጠይቀውን አክብሮ ማድረጉ ነው።የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነቱንና የዲሞክራሲ መብት መከበርን አጥብቆ ይጠይቃል፤ከርሃብና ከድህነት፣ ከስደትና ከጦርነት መገላገሉን ይመርጣል።ለዛ ብቁና ዝግጁ የሆነ መንግስትና የፖለቲካ ድርጅት የህዝቡን ልብ ሊስብ ይችላል።ለዚያ ያልታደለውን ደግሞ ሕዝቡ ዓይንህ ላፈር ይለዋል።ስልጣንም የያዘ ቢሆን ቀኑ ሲደርስ በሕዝቦች ትግል ይወገዳል።

አይውሉ ውዬ

በዚህ ርዕስ ስር ደግሞ የገጠመኝን አንድ ነገር ላጫውታችሁ፣

እንደ አጋጣሚ ከብዙ ዓመት መለያየት በኋላ ያገኘሁት አንድ አበ ልጄ የሆነ ሰው ሊጥይቀኝ ካለሁበት ይመጣል።ስንጫወት በወሬ ወሬ በእለቱ “የዲያስፖራ” ስብሰባ እንደሚካሄድ ይነግረኛል።ለምን ጉዳይ እንደሆነ ጠይቄው ፣የገጠማቸውን ችግር ለመወያየትና ሃሳብ ለሃሳብ ለመለዋወጥ እንደሆነ ይነግረኛል።በነገሩ ተነጋግረንበት አብሬው እንድሄድና ሁኔታውን እንድታዘብ ይጠይቀኛል።ለመሆኑ ተሰብሳቢዎቹ ስንት ናቸው ስለው ከሃምሳና ከአርባ አያንሱም ይለኛል።እኔም እንግዳስ በዚህ አጋጣሚ እስኪ የሚሉትን ልስማ እልና በመሄዱ እስማማለሁ።በነገራችን ላይ በዚህ “ዲያስፖራ “በሚለው አጠራር አልስማማም።በመጀመሪያ ቃሉን እንደሰማሁ ምን ትርጉም እንዳለው በተለያዩ ድህረ ገጾችና መዝገበ ቃላት/ ዲክሽነሪዎች/ ላይ የሰፈረውን ተመልክቼ ነበር።በተሰጠው ገለጻ ዲያስፖራ የሚለው ቃል በአስራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን ከክርስቶስ ልደት በፊት የይሁዳ አምልኮ ይከተሉ የነበሩ ፍልስጤማውያን/የአሁኖቹ እስራኤላውያን/ ከተማቸው በባቢሎናውያን ተወሮ፣ ቤተመቅደሳቸው ፈራርሶ  በስደትና በግዞት እንዲኖሩ የተገደዱበትን የሚያመላክት በተወሰነ ታሪካዊ ወቅት ላይ የተፈጸመን ድርጊት የሚያሳይ መሆኑን ለመረዳት ቻልኩ።ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በአጠራሩ ላይ የተለዩ ግንዛቤ ሊያድርብኝ ቻለ፤ለኢትዮጵያኑም ተገቢ መጠሪያ እንዳልሆነ ተገነዘብኩ።ምክንያቱም ምንም እንኳን ብዙ ኢትዮጵያውያን አገራችንን ለቀን በየሃገሩ ብንኖርም፣የወጣነው እራሳችን ፈቅደንና መርጠን፣ለትምህርት፣ለስራ፣ለኑሮ፣ጥቂቱም ለትግል ስለሆነ፣በተጨማሪም አገራችን በውጭ ሃይል ተወራና ተይዛ እኛ ተገደን የተባረርንና የተጋዘን አለመሆናችንን ከግምት በማስገባት “ዲያስፖራ” በሚለው አጠራር ላለመስማማት ወሰኛለሁ።ይህንን አቋሜን ይዤ ስብሰባ ከሚካህድበት ቦታ ደረስኩ።የስብሰባው ቦታ ሁለት ሽ የሚል የሚለኒየሙን በዓል የሚያመላክት ሰሌዳ ከመግቢያው ላይ የተሰቀለበት   መለስተኛ ሆቴል ነበር።ወደ ውስጥ ስንገባ የገጠመኝ እጠብቀው ከነበረው ተሰብሳቢ ብዛት በጣም ያነሰ፣በአንዱ ጠርዝ ለመስተናገድ የገቡ የሆቴሉ እንግዶች በሌላው ጥግ ደግሞ ለስብሰባው የመጡ ከሰባት የማይበልጡ ሰዎች ነበሩ። የአክብሮት አቀባበል ካደረጉልን በኋላ እንደተቀመጥን ዙሪያውን ስማትር በመካከል ኢዜአ የሚል ጽሁፍ የሰፈረበት ድምጽ  መቅረጫና ቪዲዮ  ተደግኖ አገኘሁ። ይዞኝ የሄደውን ዘወር ብዬ ምን ቦታ ነው ይዘኸኝ የመጣኸው ስለው እሱም አለማወቁን ገለጸልኝ፣ግን ሳያውቅ ቀርቶ አልነበረም፣በደንብ ያውቃል።የተመደቡት ጋዜጠኞች የስብሰባው ዓላማ “የገጠመኝ” በሚል ዕርዕስ የተሰበሰቡት የገጠማቸውን እንዲገልጹ የሚጋብዝ ነበር። ያው ከተሰበሰቡት መሃል አንዳንዶቹ ስማቸውን እየገለጹ የሚሰማቸውን አብራሩ። እንደተረዳሁት እነዚህ ተሰብሳቢዎች አማካኝ የዕድሜ ካልላቸው  ከሰላሳ አምስት እስከ ሃምሳ ቢሆን ነው፤ ሆኖም ግን የሆቴሎችና የአንድና የሁለት ፋብሪካዎች ባለቤቶች ናቸው ሲል ይዞኝ የሄደው ሹክ አለኝ።የሚያወሩት ከሞላ ጎደል በግል ስራቸው የደረሰባቸውን ሲሆን መንግስት የከፈተላቸውን ዕድል እያመሰገኑ በአግባቡ ያልተጠቀሙትን ደግሞ እያወገዙ ነበር።እንደነሱ አባባል የተሰጣቸውን መብት በመርገጥ የሃመርና የመሳሰሉት የቅንጦት ውድና ከባቢ በካይ የሆኑ መኪናዎች በስራ ስም በማስገባት እድሉ እንዲዘጋ ያደረጉ መኖራቸውን እያነሱ ሲያወግዙ ሰምቻለሁ።ከነበሩት አንዱ መንግስት ለሌሎቹ ዜጎች ማለትም ለቻይናዎች ፣ለቱርኮችና ለአረቦች እንደሚያደርገው ያድርግልን ብሎ ሲጠይቅ እኔ እጄን አውጥቼ በመጀመሪያ ከላይ በገለጽኩት ምክንያት የተነሳ “ዲያስፖራ” የሚለው አጠራር ሹመትና ደግ መጠሪያ መስሎ እንዳይታይ፣  ከኢትዮጵያኑ  አወጣጥ ጋር እንደማይጣጣም ”በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን”መባሉ በቂና ተገቢ መሆኑን በመግለጽ፣ በተጨማሪም የውጭ አገር ዜግነት ላለው “ዴያስፖራ” አገሩ ገብቶ በኢንቬስተርነት ገንዘቡን ለማዋል ከሚያስችለው መብትና ፈቃድ ውጭ በሌላው ዘርፍ፣ አገርና ሕዝብ በሚጠቅመው ጉዳይ በተለይም በፖለቲካው ተሳትፎ እንዳይኖረው በሕግ ተከልክሏል።ገንዘቡን እንጂ ጭንቅላቱን ወይም በዴሞክራሲ አገር ኑሮ የቀሰመውን የዲሞክራሲ ሕግና ባሕል በመንግስትና በሕዝብ መካከል ሊኖር የሚገባውን ግንኙነት፣የመንግስትን ና የሕዝቡን መብትና ግዴታ በስርዓቱ በመኖሩ ጥቅምና ጉዳቱን ጠንቅቆ ስለሚያውቅ በአገራችን ላይ የተዛባውን የዴሞክራሲ ስርዓት ለማስፈን በማስተማርና በማሰራጨት ሊጫወት የሚችለውን ሚና ተገፏል በማለት ብሶቴን አሰማሁ።ሁሉም ገንዘብ ይዞ አይመጣም የተሻለ አስተሳሰብና የስራ ባሕልና ዕውቀት ይዞ ለመጣውም ዕድልና በሩ መከፈት ይኖርበታል፣በሁሉም መስክ ለመሳተፍ የሚያበረታታ ሁኔታ መፈጠር አለበት አልኩ።የውይይቱ መዝጋቢ ጋዜጠኛ ንግግሬን በማቋረጥ የስብሰባው ዓላማ ይህ እንዳልሆነ በማሳሰብ ወደ ገጠመኝ ርዕስ እንድንመለስ አሳሰቡ።የእኔም ሃሳብ በግል በሚደረግ የውይይት መድረክ የሚስተናገድ እንጂ በዚህ ፕሮግራም  በይፋ እንደማይወጣና እንደማይተላለፍ ገለጹ።

በተሰበሰቡት ሰዎች ፊት ላይ የፍራቻ ገጽ ይታይ ነበር።የሚሰማውን ለመግለጽ የደፈረ አልነበረም።እኔን ይዞኝ የሄደው ሰው ብቻ በቢሮክራሲው ዙሪያ ያየውን አበሳ በማማረር ገለጸ።ሌላዋም በአገሪቱ ላይ ለውጥ መኖሩን እያጋነነች በመናገር በተለይም እኔን ለማሳመን ሞከረች።እርግጥ በመንገዶች፣በቤቶችና ሕንጻዎች፣በአንዳንድ የእንዱስተሪና

ፋብሪካ፣ሆቴሎችና መዝናኛ ቦታዎች ግንባታ ለውጥ መኖሩ ባይካድም ግለሰቧ እንደሚሉት የተጋነነ አለመሆኑን እረጋ ባለ መንፈ ለማሳየት ሞከርኩ።ሌሎቹ ድምጻቸውን አጥፍተው ተመልካቾች ነበሩ። አንዳንዶቹ በኔ ሃሳብ በመስማማት በድምጽ ሳይሆን እራስ በመነቅነቅ የግፋበት ምልክት ይሰጡኝ ነበር። ስብሰባው እንደተጠበቀው ሳይሆን ፣ከጥቂት ቆይታ በኂላ ተበተነ።ሁላችንም ወደ ምንሄድበት አቅጣጫ አመራን።የወሬ ወሬ ስሰማ የስብሰባው ዘገባ በቴሌቪዥን ፕሮግራም መተላለፉን ሰማሁ።በእለቱ እራስን ማስተዋወቅ ቢኖርም ሴሜንም ሆነ የመጣሁበትንም አገር ለመግለጽ ፈቃደኛ አልነበርኩም በዛም ሳቢያ ይሆናል ከአሜሪካ የመጣሁ ተደርጎ የተነገረው፤ ያልኩት ሳይሆን መልኬ የታየው።፤ስሜን ግን ማን እንዳሉት ሰምቶ የነገረኝ አላገኘሁም።

በጣም የሚገርመው ነገር የውጭ አገር ዜግነት ያለው ኢትዮጵያዊ በፖለቲካ ውስጥ እንዳይገባ የወሰነው መንግስት ባለስልጣኖች አብዛኛዎቹ ለብዙ ዓመታት በውጭ አገር የኖሩ፣ የውጭ አገር ዜግነትና ፓስፖርት እንደነበራቸው ወይመ ይኑራቸው ባላውቅም ከአገር አገር ለመዞር ይችሉ የነበረ መሆኑ ነው። እንግዲህ ሕጉ ለሁሉም የሚሰራ ከሆነ እነሱንም ይመለከታቸዋል ማለት ነው።እዚህ ላይ ግን በልበሰፊነት መታየት ያለበት ነገር፣ በኑሮ ምክንያት ምንም አይነት ፓስፖርት ቢይዝ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅምና እድገት የሚያበረክት ከሆነ በትውልድ ዜግነቱ በፈለገው መስክ ለመካፈል የመቻሉ መብት መታወቅ አለበት።ጥምር ዜግነት ይዘው አገራቸውን የጠቀሙ የሌላ አገር ዜጎች አስተዋጽኦ ማየቱ ትምህርት ይሆናል።ፓስፖርት ውስጣዊ ስሜትን አይገልጽም።

"ለሌላው የመዘዙት ጅራፍ ዞሮ እራስን መግረፉ አስቀድሞ ቢታወቅ ኖሮ ፣መሰንዘር ቀርቶ መግመድ ባልታሰበ ነበር።"

## አሻራና ግብር

በነበርኩበት ሰሞን ያየሁት ሌላው ጉዳይ በመላ አገሪቱ ውስጥ የትንሽም ይሁን የከፍተኛ የንግድ ፈቃድ ያላቸው ግለሰቦች በከፍተኛና በቀበሌ ጽ/ቤት እየቀረቡ አሻራ እየሰጡ፣ፎቶግራፍ እንዲነሱ፣በአዲስ መልክ ምዝገባ እንዲያካሂዱ የሚጠይቅ ትእዛዝ ወጥቶ ነበር። በወጣው ደንብ መሰረት ሁሉም እየቀረበ ለማስፈጸም የጊዜ ገደብ ነበረው።ሆኖም ግን አብዛኛው ሳይመዘገብ ቀኑ እየተቃረበ መጣ።የኛ ነገር መቸም ቀጠሮ ማክበርና በጊዜ ሰርቶ መገላገል ያዳግተናልና በቀላሉ ሊወጡት የሚቻለው ነገር፣ የጊዜ ገደቡ ሊያልቅ ቀናቶች ሲቀሩት እሩጫ ተጀመረ። ለብዙ ሰዓት መንገላታትና በወረፋ ሳቢያ ለሚነሳ ጭቅጭቅና ለእርስ በርስ ዱላ ዳረገ። የፈጠረው ውጥረትና በጊዜው አለመጠናቀቅ የተነሳ የገደቡ ጊዜ እንዲራዘም አስገደደ።

የአሻራውና የፎቶግራፉ አስፈላጊነት ፤በብዙ ቦታ ባለቤቱ ሳይታወቅና፣ግብር ሳይከፈል በመቅረቱ፣በኮንተሮ ባንድና አየር ላየር ቅብብሎሽ በአገቱ ገቢ ላይ ያስከተለውን ስብራት ለመጠገንና ለወደፊቱም ተመሳሳይ ችግር እንዳይከሰት ለመከላከል ነው ተብሎ ቢታመንም በሕዝቡ ግንዛቤ ግን መንግስት የፖለቲካ ማነቆ አድርጎ ሊጠቀምበት የሚችልበት አዲስ ወጥመድ ነው ሲል ይሰማል። በተለይም ለሚመጣው ምርጫ ማን የማን ደጋፊ መሆኑን የሚለይበት አዲስ ስልት ነው የሚለው ስጋት እያደገ ሄዷል።ያም ሆነ ይህ ሕዝቡ የተባለውን ከመፈጸም በስተቀር አማራጭ ስሌለለው በተጨማሪም በንግድ ዓለም ውስጥ የተሰማራ መክፈል የሚኖርበትን ግብር በወቅቱ የማስገባት ግዴታ ስለሚኖርበት ለዚያ ተግባርና ቁጥጥር ብቻ ከሆነ የተወሰደውን እርምጃ መቃወም አይቻልም።የነጋዴው ማህበረሰብ ሕጉንና ደንቡን ተከትሎ ማደር አለበት።መቃወም ሕጉን ሳይሆን በአሰራርና በአተረጓጎም ዙሪያ የሚታየውን ግድፈትና ጉድለት ነው።

በግብር አሰባሰቡ ላይ ፣አሰራሩ ያው እንደ ዱሮው ነው።በሀቅና በግልጽ የሚቀርብ በባለሙያ ጥናትና ምርመራ የተመዘገበ የሂሳብ አሰራር የተከተለ አይደለም።የሂሳብ ዝርዝሩም ቢቀርብ ታማኝነቱ አጠራጣሪ ነው።ነጋዴው ሲገዛና ሲሸጥ የሚያቀርበው ማስረጃና ደረሰኝ ስለማይቀርብ ገቢና ወጭውን ማመሳከር ያንንም መሰረት አድርጎ መክፈል የሚገባውን ግብር መወሰን ያዳግታል፤አይቻልም።ነጋዴው ገቢዬ ነው ብሎ ያቀረበውን መንግስት የሚያረጋግጠው ለስራው የተመደቡ ሰዎችን በሚስጥር በማሰማራት የንግድ ተቋሙን በመከታተልና የንግዱን እንቅስቃሴ በማጥናት ነው።ይህ ደግሞ ለሙስና አሰራር የተመቸ ነው።የተመደበው ታዛቢ የመሰለውን ለማቅረብ በር ይከፍትለታል። የሚሰጠው አስተያየትና ውሳኔ ከባለንግዱ ጋር በሚፈጥረው መግባባትና የጥቅም ዝምድና ላይ የተመሰረተ ይሆናል።ይህ ሊወገድ የሚችለው አላፊነትን ያገናዘበ ገቢና ወጭን የሚያሳይ የንግድ አሰራር ባህል ሲኖር ብቻ ነው።ለንግድም ስራ የሚያበቃ ችሎታና መለስተኛ ትምህርት ደረጃ ቢጨመርበት የንግድ ዘርፉንም ሆነ በንግድ ዓለም ውስጥ የሚሰማራውን ከክስረትና ከድካም ያድነዋል።

በዚሁ ዙሪያ ከአንዳንድ ነጋዴዎች የሰማሁት ትችት ቢኖር የንግድ ድርጅቱን ለማጥናት የሚላኩት ሰዎች የሚያቀርቡት ጥያቄ የንግዱን እንቅስቃሴ ብቻ የተመለከተ ሳይሆን የባለቤቱን አስተዋጽኦ፣የፖለቲካ ወይም በልማት ዙሪያ ያደረገውን ተሳትፎ በሚመለከተው ጭምር መሆኑን ነው።በጣምም የሚገርመው በልማቱ ዙሪያ በተለይ በትግራይ ልማት በኩል የተደረገ መኖሩን በግልጽ መጠየቃቸውን ሳይደብቁ የነገሩኝ አሉ።መንግስት ወይም መስሪያ ቤታቸው የሰጣቸው መመሪያ ይሁን ወይም በግል ስሜት ተነሳስተው የሚያቀርቡት ጥያቄ ይሁን የሚያረጋግጥና የሚያስተማምን ማስረጃ የለም።ወይም ነጋዴዎቹ እራሳቸው ፈጥረው የሚያወሩት ሊሆን ይችላል።እውነቱን በዙሪያው የነበሩት ሊመሰክሩ ይችላሉ።ሁሉም ነጋዴም ሆነ ሌላው አገር በሚያሳድገው የልማት እንቅስቃሴ ቢሳተፍና ለፈለገው ከባቢ ልማት ሳይገደድ የተቻለውን ቢያበረክት የሚገባና የሚያስመሰግን ስራ ነው። ሆኖም ግን መከፈል የሚኖርበት የግብር ተመን ከሚያደርገው የፖለቲካም ሆነ የልማት ተሳትፎ ጋር መያያዝ አይኖርበትም።

ይህን ጽሁፍ ከማጠቃለሌ በፊት የቅኝ አገዛዝ ስርዓት በሕዝቦች አስተሳሰብና ኑሮ ላይ ጥሎ የሚሄደውን አሻራ ለማመልከት እወዳለሁ።መነሻ የሆነኝ ከላይ የገለጽኩት በባራክ ኦባማ የተጻፈው መጽሀፍ ነው።

ቀደም ሲል በነጮች አገዛዝ ቀንበር ስር ወድቀው የነበሩ አንዳንድ ሩቅና የቅርብ ጎረቤት አገሮችን ብንቃኝ በሕዝቡ አይምሮ ውስጥ የተተከለው የዝቅተኝነትና ነጭ የማምለክ ባህሪና ልማድ እንደ ቅርስ የሚተላለፍ ጸጋ ሆኖ እናየዋለን።ለምሳሌ የቅርቧን ኬንያን ብናነሳ ፣በኬንያውያን ዘንድ ነጭ አምላክ ነው፣ነጭ አዋቂ ነው፣ነጭ ከእራስና ከጥቁር ወገን የበለጠ ክብርና ፍቅር ማግኘት የሚገባው የፍጡራን በላይ ነው።ይህን የሚያመላክት ባራክ ኦባማ የገጠማቸውን መሰረት በማድረግ በመጻህፋቸው አሳይተዋል።

ኦባማ ለመጀመሪያ ጊዜ የአባታቸው አገር የሆነችውን ኬንያን ለመጎብኘት ሄደው ነበር።ያረፉት በእህታቸው በወይዘሮ አውማ ቤት ነበር።ኦባማ የኬንያን ታሪክ በሚገባ ያውቃሉ።በእንግሊዞች ለብዙ ዓመት በቅኝ ተይዛ ከቆየች በኋላ ከዛሬ አርባ አምስት ዓመት በፊት በትግል ነጻነቷን ያገኘች አገር ነች።ምንም እንኳን ነጻ ሆና የራሷን ባንዲራ ብታውለበልብም፣ምንም እንኳን የራሷ ተወላጆች የስልጣኑ ጌታ ቢሆኑም ሕዝቡ የአገሩ ሃብት ተጠቃሚና ባለቤት አልሆነም።ሁሉም የገቢ ምንጭ የሆነው፣ሰፋፊ የእርሻ መሬት፣ትልቅና ትንሽ የምርት ድርጅቶች፣ታላላቅ ሆቴሎችና ባንኮች የነጮችና የጥቂት ባለስልጣኖች ይዞታ ነው።ነጮች የንብረቱ ባለቤቶች ብቻ ሳይሆኑ ጥቁር ኬንያዊ እንደፈለጉ የሚያደርጉትና የሚያሽከረክሩት የግል ይዞታቸው ነው።አክብሮና አደግድጎ፣ሲቆነጥጡት ወይም ሲቆጡት እያሞገሰና እየሳቀ መቀበል ግዴታው ነው።ነጮች የፈለጉትን ለማድረግ የሚችሉባት አገር ስለሆነች ኬንያ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የሰላምና የዲሞክራሲ ምልክትና ምሳሌ ተደርጋ ትቆጠር ነበር።ሕዝቡ እንዳያምጽ ከጅ ወዳፍ በሆነ እርዳታ፣በፖሊስ ሃይልና በቁጥጥራቸው ስር በሆነው የፍትህ ተቋምና ባሰለጠኑዋቸው የጥቁር ነጭ መሪዎቹ እየተደለለ የበታችነቱን ተቀብሎ ሰጥ ለጥ ብሎ እንዲያድር አድርገውታል።በዚያ ላይ ሙስና የኬንያውያን የስራ ማንቀሳቀሻ ሞተር ነው።ባራክ ኦባማ ይህንን በይበልጥ የተገነዘቡት አንድ ቀን ከእህታቸው ጋር የናይሮቢን ከተማ እየተዘዋወሩ ባዩበትና እግረ መንገዳቸውን ነጮች በብዛት ገብተው ከሚዝናኑበት ሬስቶራንቶችና ሆቴሎች በአንዱ ጎራ ባሉበት ወቅት ነበር።

እንደማንኛውም ተስተናጋጅ ቦታ ይዘው የአስተናጋጁን መምጣት በመጠባበቅ ብዙ ደቂቃዎች አሳለፉ።ከነሱ በኋላ የገቡ ነጮች ቦታ ከመያዛቸው ሁለት ጠብደል አስተናጋጆች ተሽቀዳድመው አንዱ ፈጥኖ የተጠጋው ትዕዛዝ ተቀብሎ ወዲያው የፈለጉት ቀርቦላቸው ሲበሉና ሲጠጡ፣ኦባማና እህታቸውን ያስተናግዳቸው ቀርቶ ዘወር ብሎም ያያቸው አልነበረም።ነገሩ ግራ ገብቷቸው ደጋግመው የእጅ ምልክት እየሰጡ ቢጠሩም አውቆ የተኛ ነውና ጥያቄያቸውን የሚሰማ ፈቃደኛ አንድም አስተናጋጅ አልነበረም።ውስጣቸው እየደበነ ከብዙ ሙከራ በኋላ አንድ ከሌሎቹ በዕድሜ ጠና ያለ አስተናጋጅ እየተለጠጠ ቀርቦ የምርጫ ደብተሩን አስቀምጦላቸው ትዕዛዝ ሳይቀበል ተመለሰ።ወንድምና እህት ከአሁን አሁን ተመልሶ ያስተናግደናል ብለው ቢጠብቁ ሳይመለስ ቀረ።ሁኔታውን የተረዱት የኦባማ እህት፣አውማ ትዕግስታቸው አለቀና እንግዳ ወንድማቸውን ኦባማን እንውጣ ብለው ከተቀመጡበት ተነሱ።ወደ በሩ ከመጠጋታቸው በፊት በንቀት ይመለከታቸው ወደ ነበረው አስተናጋጅ መለስ አሉና “በጣም ልታፍር ይገባሃል” ሲሉት በስዋሂሊ ቋንቋ መልስ እየሰጠ ተርጎመጎመ።አውማ በመቀጠል “ስንት ቤተሰብ እንደምትቀልብ ደንታዬ አይደለም ግን የራስህን ወገኖች እንደውሻ ማየትና መናቅ አይኖርብህም፣ተዋርደህ ወገኖችህን ታዋርዳለህ” አሉና ቦርሳቸውን ከፍተው “ተመልከት፣እኔም እንደሌሎቹ ነጮች ለተጠቀምኩበት ሁሉ የምከፍለው ገንዘብ አለኝ”ብለው የብዙ መቶዎች ጥራዝ አሳይተውት ፣አንዷን ነጠላ ብር አውጥተው ከመሬት ላይ ወርውረውለት ወጡ።በብስጭት ወዴት አቅጣጫ እንደሚሄዱ ባለማወቅ እረጂም መንገድ ከተጓዙ በኋላ፣በሁኔታው የተገረሙት ባራክ ኦባማ በዋናው መንገድ ዳር ከፖስታው ቤት ፊት ለፊት ከሚገኘው አግዳሚ ወንበር ላይ ለመቀመጥ አሳብ አቀረቡና አረፍ ብለው ወጭ ወራጁንና የትራፊኩን ግርግር ይታዘቡ ጀመር።

እህት አውማ ቦርሳቸውን አስቀመጡና በረጂሙ ተንፍሰው ገንዘብ እንደዚያ አድርገው መወርወር እንደማይገባቸው በማጤን ፤ለዚያ ያስገደዳቸውን ለወንድማቸው ለማስረዳት ጀመሩ።

እንደዚህ ከመሰለው ሆቴልና የመዝናኛ ክበቦችም ሆነ ትላልቅ መስሪያ ቤቶች ብቻየንም ሆነ ከሌላ ጥቁር ጓደኛዬ ጋር ሁኜ ለመግባት አይፈቀድልኝም፤እከለከላለሁ።ግን ከአንድ ሽማግሌ ፈረንጅ ጋር ከሆንኩኝ "ጤና ይስጥልኝ የእኔ እመቤት "እባልና ከጆሮ ጥግ እስከ ጆሮ ጥግ በሚደርስ ፈገግታ እስተናገዳለሁ።የአገሪቱ ገቢ አደገ ቢባልም፣ብዙ ነገር መግዛት ብትችልም፤ኬንያ የሌሎች አፍሪካውያን ማፈሪያና መሳቂያ ነች፤ኬንያ ለነጮች ፍርፋሪ እግሯን ከፍታ የምትሰጥ ሸርሙጣ ማለት ነች እያሉ እንባ እየተናነቃቸው ብሶታቸውን ለወንድማቸው ሲገልጹ፣ወንድማቸው በሁሉም ቦታና አገር የሚኖርና ያለ ከድህነት ጋር የተያያዘ በሽታ መሆኑን እየገለጹ ለማጽናናት ሞከሩ።

ኢትዮጵያ ሕዝብ በተከታታይ ታሪኩ የነጮችን የቅኝ አገዛዝ ሙከራ እምቢ አሻፈረኝ ብሎ ድባቅ የከተተ ነው።የዚህ እምቢ ባይነት በቀል በልዩ ልዩ ገጽ ሲንጸባረቅ ቆይቷል፤ አሁንም ወዳጅ መስለው፣በነጻነትና በኩልነት ስም ከየተገንጣዩ ጀርባ ተሰልፈው በመግባት የህዝቡን አንድነት ሲፈታተኑት ይታያሉ።የኢትዮጵያ ሕዝብ የነጮች የበታች ሆኖ ለማደር ዝግጁና ህሊናው ፈቃደኛ አይደለም።ለገንዘብና ለጊዜያዊ ጥቅም ብሄራዊ ክብሩን አሳልፎ አይሰጥም፤አሳልፈው የሚሰጡ ካሉ ይቋቋማቸዋል።በሕዝቡ ኑሮ ላይ የተከሰተው ችግር፣የግሎባላይዜሽን መርሆና በልማት ሽፋን የተከፈተው በር የአረቦችን የሃይማኖት ማስፋፋት ፍላጎትና የነጮችን የእጅ አዙር የቅኝ አገዛዝን የሚጋብዝ መሆን አይኖርበትም።

ከአስራ አራት ዓመት በፊት በሴፕቴምበር ወር 1995 የጻፍኩትን የግጥም መልዕክት በማካተት የትዝብትን አምድ እደመድማለሁ።

## አንድነት

በምስራቅ በምዕራብ

በሰሜን በደቡብ

በለንበት ዓለም

ክርስቲያን ከክርስቲያኑ እስላሙ ከእስላም

እርስ በርሱ ሲናቆር ሕዝብ ሲተላለቅ

አልጀሪያ ሲታሽ ዩጎዝላቪያ ሲደቅ

አይርላንድ ሲታመስ ኢጅብት ሲጨነቅ

አገር ሲፈራርስ ተያይዞ ሲወድቅ

ሩዋንዳ በዘር ሶማሌ በጎሳ

ተከፋፍሎ ሲያልቅ ጦርነት ሲያነሳ

ደካማው ሕጻኑ ሲቆጥር አበሳ

ትርፉ መተላለቅ

ተያይዞ መውደቅ

መሆኑን እንወቅ።

ችግር ድንቁርና በሽታ ላይጠፋ

በዘር መከፋፈል አይጠቅምም አንልፋ

የጅ አዙር አገዛዝ የፈጠረው ፈሊጥ

በዘርና በምነት ሕዝብን ማበጣበጥ

ሕዝብ እያጋደለ አገር እየናደ ጦር መሳሪያ መሸጥ።

ለጠላት ድጎማ እራስን አዋርዶ

ከሰላማዊ ለውጥ የጦር ሜዳ ወዶ

ሕዝብን ማጨፋጨፍ ታሪክን አስከዶ።

በራስ መተማመን መመካቱ ቀርቶ

የማይገባ ፈሊጥ ከጠላት አምጥቶ

ሕዝብ እንዳይግባባ መሰናክል ሰርቶ

ያገር ቅርስ ታሪክ ድራሹን አጥፍቶ

መባከን ማባከን ድርጅት መስርቶ።

እስኪ ተመልከቱት ይህን አስተዳደር

ሕዝብ እንዳይስማማ ተከፋፍሎ እንዲኖር

የሰሜኑ ደቡብ የደቡቡ ሰሜን

የምዕራቡ ምስራቅ የምስራቁ ምዕራብ

እንዳይጠያየቅ እንዳይቀራረብ

እንደ ልቡ እንዳይዞር

እንዳሻው እንዳይኖር

በተወለደበት ፣በአንድ ጠባብ ቦታ ተወስኖ እንዲቀር

የጋራ መግባቢያ ቋንቋ እንዳይናገር

እዩት ተመልከቱት የባቢሎን ታሪክ ዳግመኛ ሲዘከር።

ከልልና ቋንቋ አድርጎ መለያ

ትንሽ መንደር መፍጠር ቀርታ ኢትዮጵያ

ሆኗል ባገራችን የዘመኑ ሙያ።

እስኪ ተመልከቱት ያገር ልጅ ሲለፋ

ባንዲራውን ቀዶ ባንዲራ ሲሰፋ

የሁላችን አርማ ባንዲራው ምን አለ

አገር አልበደለ፣ወይ ሰው አልገደለ

ቀለሙ ከሆነ ያስቀየመው ነገር

ሌላ ለመለወጥ ባንድ ላይ እንምከር

ስርዓት ባጠፋ

መሪ በበደለ

አይጠላም አርማ፣አይጠላም ወገን ፣አይጠላም አገር።

በብሄር ነጻነት በእኩልነት ስም

የአገር ህልውና፣

የህዝቦች ዝምድና

አይገረሰስም፣አይደመሰስም።

ይዞ ከማውለብለብ የግል ባንዲራ

አንድነት መስርቶ መታገል በጋራ

የሕዝብ እኩልነት ሙብት ቢታወቅም

አገር ግንድ አይደለም አይሰነጠቅም።

የቋንቋ ልዩነት ቢኖርም ባይኖርም

አገር የጋራ ነው፣ሕዝብ አይበጠርም።

ጥላቻ ሲነግስ ቂም በቀል ሲስፋፋ

አንተም ተው፤ አንተም ተው፤ የሚል ሽማግሌ አስታራቂ ጠፋ።

የቱ ሽማግሌ አስታርቅ ይባላል?

የሃይማኖት መሪም እርስ በርሱ ይባላል

የጥፋቱ መንገድ፣ ይቀልበስ ይታጠፍ

ለሰላም ለእድገት አብረን እንሰለፍ።

ከሰሞኑ መጫጭሮቼ ደግሞ ይችን ጀባ እላለሁ

ካልተገላበጠ ካልተሽከረከረ፣

ታፍኖ ታቅቦ ተዘግቶ ከኖረ፣

ውሃም ይገለማል፣

መልኩን ይለውጣል፣

ፈሳሽ መርዝ ይሆናል፣

በመጥቀሙ ምትክ ይጎዳል፣ይገላል።

መርዘኛ ትላትል እንዳይራባበት

ውሃ መንቀሳቀስ መሽከርከር አለበት።

መንግስትም እንዲሁ ካልተቀያየረ

አንዱ እንደፈቀደው በጉልበት ከኖረ፣

ሕዝብም ይሰለቻል፣

ለአምባ ገነንነት

ለእርስ በርስ ግጭት፣

ለዝርፊያ ያመቻል።

አገራችን የገጠማትን ፈተና አልፋ ሌሎች አገሮች ከደረሱበት ደረጃ ለመድረስ እንድትበቃ የቀና አሳቢዎች እምነትና ፍላጎት ነው።

ጊዜ ያንን ለማየት ያብቃን!!!!

አገሬ አዲስ

ሆፍ ዶርፕ፣ሆላንድ

ማሳሰቢያ

በሚመጡት ወራቶች በኢትዮጵያ፣በኬንያና በኡጋንዳ ከመቸውም በከፋ ሁኔታ በሃያ ሶስት ሚሊዮን ሕዝብ ላይ ከፍተኛ አደጋና የከባቢ ቀውስ ሊያስከትል የሚችል የርሃብ መቅሰፍት ማንዣበቡን የሚጠቁም አክስፋም(oxfam) የሚባለው ዓለም አቀፍ የርዳታ ድርጅት መግለጫና ጥሪ አስተላልፏል።

በዚህ እንደመታወቂያችን ቋሚ ሆኖ ስናፍርበት ለኖረው፣ ችግር ከመቸውም በበለጠ ለዘለቄታው ችግሩ የሚወገድበትን ዘዴና ብልሃት የመሻቱ ተግባር የሁሉም ስለሆነ፣መንግስትም ተቃዋሚም ለስልጣን የሚያደርጉትን ሽኩቻ ለጊዜው ወደ ጎን ትተው በዚህ አሳሳቢና አስቸኳይ ጉዳይ ላይ እንዲረባረቡ የበኩሌን ጥሪ አደርጋለሁ። እርሃቡን የፖለቲካ መሳሪያ እንዳያደርጉት አደራ እላለሁ።በውጭና በውስጥ የሚኖረውም ኢትዮጵያዊ ለዚህ ሰብአዊና ብሄራዊ ጉዳት በቅድሚያ ዝግጅትና እርዳታ የማሰባሰብ እርምጃ እንዲወስዱ አሳስባለሁ።አለበለዚያ ሰርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ ይሆናል።የአለም አቀፍ ድርጅቶችንና መንግስታትን እጅና እርዳታ ከመጠየቃችን በፊት እራሳችን ማድረግ የሚኖርብንን ግዳጅ መወጣት ይኖርብናል።ተጎጂና ተጠቃሚው ደሃው ሕዝብ ነው። በዘመነ ደርግ ጊዜ የተፈጸመው ስህተት መልሶ እንዳይደገም መጠንቀቅ አለብን።